የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Health






# በኢትዮጵያ ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት ደረጃዉን የጠበቀ የአተገባበር ሥርዓት ሰነድ








የካቲት 2008

# ማውጫ

ምስጋና ---------------------------------------------------------------------------------------------------- II
መግቢያ---------------------------------------------------------------------------------------------------- III

ክፍል- 1

ወሲባዊ ጥቃት ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 1

1.1 መነሻ ሀሳብ ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 1
1.2 የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ---------------------------------------------------------------------------------- 2
1.3 የሰነዱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ---------------------------------------------------------------------------- 4

ክፍል-2

ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ ወሰን እና የአገልግሎት ጣቢያ ---------------------------------------------------------- 5

2.1 ራዕይና ተልዕኮ ---------------------------------------------------------------------------------------------- 5
2.2 ዓላማ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 5
2.3 የሰነዱ ወሰን ---------------------------------------------------------------------------------------------- 6
2.4 የአገልግሎት ጣቢያዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ------------------------------------ 7

ክፍል-3

ትርጉም፣ መርሆዎች፣ ሪፖርት አዘገጃጀት፣ የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአትና የድጋፍ ፈላጊዎች አካሄድ -------- 8

3.1 የቁልፍ ቃላት ትርጉም ---------------------------------------------------------------------------------- 8
3.2 መርሆዎች ---------------------------------------------------------------------------------------------- 10
3.3 ሪፖርት ማድረግና የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአት -------------------------------------- 13

ክፍል-4

ለወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች የምላሽ ሰጪ አካላት የአሰራር ሂደት ---------------------------------------------- 15

4.1. አጠቃላይ የአካላት ምላሽ አሰጣጥ ---------------------------------------------------------------- 15
4.2. ተቋማዊ ልዩ ምላሽ ---------------------------------------------------------------------------------- 20
4.3. ተጎጂዎች የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ (የአንድ መስኮት አገልግሎት) የሚያገኙበት አካሄድ --------- 33

ክፍል-5

ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል ---------------------------------------------------------------------------------- 36

5.1. መከላከል ---------------------------------------------------------------------------------------------- 36
5.2. በጤናው ዘርፍ ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል ---------------------------------------------------------- 37
5.3. ይሄንን ደረጃውን የጠበቀ የአተገባበር ስርአት ሰነድ ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ ----------------- 38

እዝል

እዝል-1 ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 39
እዝል-2 ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 40
እዝል- 3 ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 42

# ምስጋና

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይሄንን በኢትዮጵያ ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት ደረጃውን የጠበቀ የአተገባበር ስርአት ሰነድ ለማዘጋጀት ወርቃማ ጊዜያችሁን እና እውቀታችሁን ላበረከታችሁ ስማችሁ ከዚህ በታች በክብር ለተዘረዘረው አማካሪዎችና ባለሙያዎች የከበረ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

1. ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
   - 1.1 ወ/ሮ ያምሮት አንዱአለም
   - 1.2 ዶ/ር መንግስቱ ኃ/ማሪያም
2. ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
   - 2.1 ሰላማዊት ግርማይ
   - 2.2 ማህሌት ገ/የሱስ
   - 2.3 ፋሲካ ሃይሉ
3. ከፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት
   - 3.1 አቶ ልውለስላሜ ሊበን
4. ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር
   - 4.1. አቶ ስለሺ ታደሰ
   - 4.2. አቶ ኃይለልዑል ስዩም
   - 4.3. አቶ ደረጀ ተግይበሉ
5. ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
   - 5.1. ኮማንደር ፀሀይነሽ መስፍን
6. ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን
   - 6.1. ኮማንደር አፀደ ወርዶፋ
7. ከኢትዮጵያ የፅንስና የማህፀን ሃኪሞች ማህበር
   - 7.1. ዶ/ር ደሴ እንግዳየሁ
   - 7.2. ዶ/ር ዳዊት ደሳለኝ
8. ችፎረም ፎር ሰስቴናብል ቻይልድ ኢምፓወርመን
   - 8.1 አቶ መኮንን በለጠ

በተጨማሪ ለዚህ ሰነድ ዝግጅት የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ላደረጋችሁልን ለሮያል ኔዘርላንድ ኤምባሲ፣ በተባበሩት መንግስታት የስነሕዝብና ስነተዋልዶ ጤና ድርጅት (UNFPA)፣ ለኢትዮጵያ የፅንስና የማህፀን ሃኪሞች ማህበር (ESOG) በፌዴራል ጤ ጥበቃ ሚኒስቴር ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ከሰተብርሃን አድማሱ (MD, MPH)
የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር

# መግቢያ

ወሲባዊ ጥቃት ዓለም አቀፍ ስጋት ሲሆን በማንኛውም ሰው ላይ እድሜ፣ የኑሮ ደረጃ፣ ብሄርና ፖለቲካዊ አመለካከት ሳይወስነው በሰብአዊ መብት፣ በጤና፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሕይወት ላይ ቀውስ የሚያስከትል ስር የሰደደ መጥፎ ምግባር ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም የህብረተሰብ አካላት ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ሕብረት ፈጥረው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ መጥፎ ምግባር በተዛባ አመለካከትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተሸፋፍኖና ተሰውሮ የኖረ በመሆኑ በአንድ በተወሰነ ጊዜና ቦታ በተናጠል በሚደረግ እንቅስቃሴና ጥረት የሚወገድ ሳይሆን ሁሉም የማህበረሰብ አካላት ያላቸውን አቅምና ጊዜ በማስተባበርና በማቀናጀት የመግባባት (የግብብነት) መድረክ ፈጥረው ሊታገሉት የሚገባ ማህበራዊ ጉዳይ ነው፡፡

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳትና ትኩረት በመስጠት ይሄን ደረጃውን የጠበቀ የአተገባበር ስርአት ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የማስተባበሩንና አመራር የመስጠቱን ሀላፊነት በቀዳሚነት ቢወስድም በተናጠል የሚደረገው እንቅስቃሴ ከሚፈለገው የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ለመድረስም ሆነ የተጠቂዎቹን ፍላጎት ለማሟላት እንደማያስችል ግልጽ ነው፡፡

በመሆኑም ሚኒስቴሩ ከሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽንና ማህበረሰባዊ የስነ ልቦና አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር ሕብረት በመፍጠርና ከአካላቱ በተውጣጡ ባለሙያዎች ሰነዱ ተዘጋጅቶ ሊቀርብ ችሏል፡፡ ሰነዱ በሁሉም አካላት መካከል ትስስርን በመፍጠር ለደንቡና ለመመሪያው ተገዢ ሆነው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት እንዲችሉ ዝርዝር ተግባራትን የሚያመላክት ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

ሰነዱ አምስት ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የወሲባዊ ጥቃትን የስርጭት ደረጃና በሚያሳድራቸው ተፅእኖዎች ዙሪያ መረጃዎችን በማቅረብ የሰነዱን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ፣ አለማቀፋዊና ብሄራዊ ፖሊሲዎችን ከህግ ማዕቀፎች ጋር በማብራራት ይቀርባል፡፡ በሁለተኛው ክፍል ራዕዩን፣ ተልዕኮውን፣ አላማውንና የትኩረት አቅጣጫዎቹ ይቀርባሉ፡፡ በማስከተል የቁልፍ ቃላት ትርጉም፣ የአተገባበር መርሆዎች፣ የወሲባዊ ጥቃት ሪፖርት አዘገጃጀትና ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ግለሰቦች የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአትና ድጋፍ ፈላጊዎች አገልግሎት ለማግኘት መከተል በሚገባቸው ሂደት ዙሪያ በክፍል ሶስት ይብራራሉ፡፡ በአራተኛው ክፍል ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የዘርፈ-ብዙ ምላሽ አሰጣጥ ስርአት ላይ የሚያተኩር ሲሆን በአምስተኛውና በመጨረሻው ክፍል ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከል በሚተገበሩ አሰራሮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

# ክፍል- 1
# ወሲባዊ ጥቃት

1

## 1.1 መነሻ ሀሳብ

ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት "በሴቶችም በወንዶችም ላይ የሚፈጸም ጥቃት ሲሆን በአብዛኛው ሴቷ ተጎጂ የምትሆንበት ሆኖ በሴቶችና በወንዶች ማህበራዊ ግንኙነት ማካከል የተመጣጠነ የሀይል ሚዛን ካለመኖር ይመነጫል፡፡" (ሳራ ቦት፤2004) የተባበሩ መንግስታት በሴቶች ላይ የሚፈፀምን ጥቃት ለማስወገድ ባወጣው ድንጋጌ መሰረት የሴቶች ጥቃት ማለት "ማንኛውም አይነት ጾታን መሰረት አድርጎ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ወይንም ሊደርስ የሚችል፤ የአካል ጉዳት፣ ወሲባዊ ወይንም ስነልቦናዊ የሆነ ስቃይ፤ ድርጊቱ የሚያደርሰውን ስጋት አካቶ አቅም የሌላቸውን ንጹሀን ሴቶች ነጻነት በመግፈፍ በማስገደድ ወይንም ጉልበትንና ስልጣንን በመጠቀም በአደባባይ ወይንም በስውር በግላዊ ሕይወታቸው ላይ የሚፈጸም ጥቃት ማለት ነው፡፡"

የሴቶች ጥቃት ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ያለው ሲሆን በሴቶችና በወንዶች መካከል የሀይል ሚዛን እና እኩልነት ባልተጠበቀበት ስርአት ውስጥ ስር የሰደደና የከፋ ሆኖ ይገኛል፡፡ ችግሩ የሁሉም አገሮች ችግር ሆኖ ሰብአዊ መብትንና የጾታ እኩልነትን ለማስፈን የሚደረግን ጥረት በማወክ ተንሰራፍቶ የሚገኝ ነው፡፡ በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት በርካታ ገጽታዎች ያሉት ሲሆን እርስ በእርሳቸው በተሳሰሩና አንዳንድ ጊዜም በተደጋጋሚ በሚከሰቱ ተከታታይነት ባላቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ይገለጣል፡፡ የሚፈጸመው ወንጀል የአካል፣ የወሲባዊና የስነልቦና ጥቃት እንዲሁም የኢኮኖሚ ጭቆናና ብዝበዛን ያካትታል፡፡ ወሲባዊ ጥቃት የትኛውንም አይነት ወሲባዊ ድርጊት ከአንድ ሰው ፍላጎት በተፃራሪ በህገወጥ መንገድ የሚፈጸም በርካታ ፀያፍ ድርጊቶችን ያካተተ ሲሆን በወንዱ ብልት የሴቷን ብልት አካባቢ መነካካት፣ ወይንም በወንዱ ብልት የሴቷን መቀመጫ አካባቢ መነካካት ወይንም በፊንጢጣ ብልትን መክተት፣ በአፍና በወንዱ ብልት ንክኪ መፍጠር፣ በሴቷ ብልት አካባቢ ወይንም በፊንጢጣ፣ ወይንም በሌላው ሰው የመራቢያ አካል ወይንም በፊንጢጣ ውስጥ እጅን፣ ጣትን ወይንም ሌላ ቁስ አካልን ሆን ብሎ መጨመር፣ በቀጥታም ሆነ በአልባሳት ላይ በመራቢያ አካላት አካባቢ፣ በቂጥ፣ በእንብርት አካባቢ፣ ጡትን ፣ መቀመጫን ወይንም የማንኛውንም ሰው ከሱ ወይንም ከሷ ስምምነት ውጪ ወይንም ስምምነት ለማድረግም ሆነ ድርጊቱን ለመቃወም በማይችል ሰው ላይ የሚፈጸም ሆኖ ጾታዊ ንዝንዝና ማስጨነቅን ያካትታል፡፡ ሴቶች ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ ጥቃት በተለያዩ ቦታዎችና ሁኔታዎች ውስጥ የሚከሰት ሲሆን በአሁኑ ወቅት ችግሩ ድንበር ተሻጋሪ እየሆነ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ወሲባዊ ጥቃት ከሰብአዊ መብት፣ ከማህበረሰብ ጤና፣ ከእድገትና ከኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር የተሳሰረ ጉዳይ ነው፡፡

## 1.2 የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ

ኢትዮጵያ በህዝብ ብዛት ከአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሲሆን 84.9 ሚሊዮን ህዝብ ያላት አገር ናት፡፡ በከተሞች እድገት በዓለም ከሰለጠኑ አገሮች ጋር ስትነጻጸር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ አገር ስትሆን 83.6 በመቶ የሚሆነው ሕዝቧ በገጠር ይኖራል፡፡ ከአጠቃላይ የህዝብ ቁጥሯ 49.5 በመቶ ሴቶች ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ 24 በመቶው በመውለድ እድሚያቸው (ከ15-49 አመት) ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ ከአጠቃላይ ህዝቧ ከፍተኛውን ቁጥር (44.9 በመቶ) የሚሸፍኑት እድሜያቸው ከ15 አመት በታች የሆኑ ወጣቶች ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት የመውለድ መጠን እየቀነሰ የአንዲት ሴት የመውለድ መጠን 4.8 ውልደት በ2010 እ.ኤ.አ ቢሆንም የአገሪቱ አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ ከፍተኛ የወጣቶች ቁጥር በልጅ መውለድ እድሜ ውስጥ ሆነው ይታያል፡፡

ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን ሴቶች በአገሪቱ አጠቃላይ እድገት ላይ ቁልፍ ሚና እየተጫወቱ ያሉ ቢሆንም ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ማህበራዊ የፍትህ እጦትና የጥቃት ጫና ያረፈባቸው ሆነው ይገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታውን በጥልቀት ለመረዳት የሚያስችል ከፍተኛ የመረጃ እጥረት መኖሩ እንዳለ ሆኖ በሴቶች ላይ የሚደርሱ የሁሉም አይነት ጥቃቶችን አይነትና ስርጭቱን ለማወቅ የተካሄዱ ውስን ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ችግሩ በተለያዩ መንገዶችና ደረጃዎች በከተማም ሆነ በገጠር እየተስፋፋ መሆኑን ነው፡፡ በተጨባጭ የሚገኙ መረጃዎች እንዲሚያሳዩት ደግሞ በሴቶችና በታዳጊ ልጃገረዶች ላይ የሚደርሱ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ከፍተኛውን ቁጥር የሚሸፍኑ ሲሆን በኢትዮጵያ በሴቶችና በልጆች ላይ ለሚደርሱ ጥቃቶች መገለጫዎች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በዓለም አቀፍና በአገር ውስጥ የዜጎቹን ደህንነት ለማሻሻልና ለማስጠበቅ ባለው ቁርጠኝነት የማህበራዊና የጾታዊ ስርአት ለውጥ ለማስመዝገብ የሚረዱ ፖሊሲዎችና የህግ ድንጋጌዎች በመዘጋጀት ተቋማዊና ስልታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ የመንግስት የለውጥ ትኩረት አቅጣጫዎች ከሁለት ስልታዊ ጉዳዮች ጋር የተሳሰሩ ሲሆኑ የመጀመሪያው በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታየው ጾታዊ ጥቃት ስር የሰደደ የጾታ እኩልነት ያለመከበር ውጤት መሆኑና ሁለተኛው እነኝህ ጾታዊ ጥቃቶች በግልጽ ከሚታየው አስከፊ ድህነት ጋር ተያያዥነትና ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን ታሳቢ ያደርጋል፡፡

### የሕግ ማዕቀፍ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የሴቶችን መብት ለማስከበር ባለው ቁርጠኝነት በአገሪቱ ሕገመንግስት እና በሌሎችም የሕግ መዕቀፎች ውስጥ ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ ህገመንግስቱ በመሰረታዊነት ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች እኩል መብት የሰጠ ሲሆን ፆታን መሰረት ያደረገ ልዩነትን ይከላከላል፡፡ ሕገመንግስቱ የሴቶችን ልዩ ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ በአንቀጽ 35 ልዩ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን መብት አጎናጽፏል፡፡

በተጨማሪ የፆታ እኩልነትን በማስፈን በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመዋጋት በተለያዩ ፖሊሲዎችና የስትራተጂ ሰነዶች ውስጥ እውቅና እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ በብሄራዊ የሴቶች ፖሊሲ (እ.ኤ.አ.1993) ፣ የኢትዮጵያ ሴቶች የልማትና የለውጥ ፓኬጅ (እ.ኤ.አ. 2006)፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ በተዘጋጀው ብሄራዊ ስትራተጂ ሰነድና በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (እ.ኤ.አ. 2010) በመሳሰሉ ሰነዶች ውስጥ ተንጸባርቀው ይገኛሉ፡፡ ተሻሽሎ የወጣው የአገሪቱ የወንጀል ሕግና የቤተሰብ ሕግ በተለየ ሁኔታ በሴቶች ላይ ለሚደርሱ ጥቃቶች ከለላ የሚሰጡ ናቸው፡፡

በሕግ አውጪው አካል ደረጃ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መንግስት በተለያዩ የአስተዳደር ደረጃዎች የሴቶችና የህጻናት ጉዳይ ቋሚ የፓርላማ ኮሚቴ እንዲያቋቁሙ በማድረግ ጾታን ማዕከል ያደረጉ ሕጎች መተግበራቸውን፣ ፆታን ማዕከል ያደረጉ ዝግጅቶች እንዲቀርቡ፣ የሴቶችን አቅም ለማጎልበትና የጾታ እኩልነት በተመጣጠነ ደረጃ እንዲሰፍን የሚያስችል በጀት እንዲመደብ መደረጉን ይከታተላል፡፡ በሕግ አስፈጻሚው ደረጃም የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር በፌዴራል ደረጃ በአዋጅ ቁጥር 916/2008 እ.ኤ.አ. በድጋሚ በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሌሎች አካላት መካከል ህብረት በመፍጠርና የሚመለከታቸው አካላት በብሄራዊ ደረጃ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ሁሉንም አይነት ጥቃቶች ለመከላከልና ብሎም ለማስወገድ ያካበቱትን ልምድና ተሞክሮ አቀናጅቶ በመቀመርና አቅምን በማጎልበትእንዲሰራ በሕግ የተደገፈ ስልጣን ተሰጥቶታል። ግንኙነት ያላቸው የክልል ቢሮዎች እና የወረዳ ጽህፈት ቤቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ በድጋሜ ተጠናክረው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ የሴቶች ድምጽ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሴቶች ሕጻናትና ጉዳይ ሚኒስቴር አማካይነት የተወከለ ሲሆን በክልል ምክር ቤቶች ደረጃ በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ቢሮ ሲወከል በወረዳ ካቢኔ ደረጃ በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት ይወከላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በውስጡ የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ክፍል ያቋቋመ ሲሆን ተቋሙን ማእከል ያደረጉ ከጾታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በመከታተል ያስፈጽማሉ፡፡ እያንዳንዱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በተዋረድ በክልልና በወረዳ ደረጃ በስሩ በተደራጁ ቢሮዎችና ጽህፈት ቤቶች ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ያደራጃል፡፡

የጤናውን ሴክተር በተመለከተ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች እንክብካቤ ለማድረግ የሚረዳ አገር አቀፍ የሆነ የአሰራር፣ የአመራርና የስልጠና ሰነድ በ2009 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ተዘጋጅቶ የሕክምና አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ወሲባዊ ጥቃትን በተመለከተ የህክምና ትምህርት ቤቶች ከትምህርት መርሀ-ግብሩ ጋር ተቀናጅቶ እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ተደርጓል፡፡ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ሞዴል ክሊኒኮች በጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ በአዳማ ሪፈራል ሆስፒታልና በሃዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል ውስጥ ተቋቁመዋል፡፡

የፍትህ ሴክተሩም ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ህጻናት ጉዳይ የሚያስተናግድ ለተጎጂዎቹ ምቹ የሆነ አሰራር ያላቸው ልዩ ችሎቶች እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ልዩ ችሎቶች በተጎጂዎቹና በፍርድ ቤቱ መካከል ሆነው ጉዳዩን የሚያስተላልፉ በማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የሚታገዝ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የፌዴራል አቃቤ ሕግ ፍትህ ጽ/ቤቶች የሴቶችንና የህጻናትን ጥቃት የመመርመርና ውሳኔ የሚያሰጥ ቡድን አቋቁመዋል፡፡ የፖሊስ የሴቶችና የህጻናት ልዩ የጥበቃ ማዕከላት ለወሲባዊ ጥቃት ሰለባዎች ልዩ የጥበቃ አገልግሎት ለመስጠት ተቋቁመዋል፡፡

## 1.3 የሰነዱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ

ከወሲባዊ ጥቃት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጁ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ወሳኝ በሆነ ደረጃ የህግ፣ የጤናና ማህበረሰባዊ የስነልቦና አገልግሎቶችንና ማናቸውንም ከተጠቂዎች ህይወት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሁኔታዎች ለመድረስና ለውጥ ማምጣት በሚቻልበት ደረጃ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ይሄም በመሆኑ አንድ አካል በተናጠል መድረስ ከሚችለው በበለጠ የሚጠበቀውን ምላሽ መስጠት ያስችላል ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም በአገሪቱ ለአሰራር ምቹ የሆኑ የፖሊሲና የህግ ዝግጅቶች ቢኖሩም ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከል የሚያስችል የግንዛቤ ማነስና የህግ አፈጻጸም ችግር ይታያል፡ ፡ በህግ አስፈጻሚው፣ በጤና ፣ በፖሊስ፣ በማህበረሰባዊ ስነልቦና ፣ በመገናኛ ብዙሀን፣ በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይና በሌሎችም አካላት መካከል የተደረገው ውይይት እንዳመላከተው ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችና ደንቦች አለመኖር አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ጠቀሜታ ያላቸው ባለድርሻ አካላት ሕብረት ፈጥረው ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ አላስቻለም፡፡ ሁኔታው በጤና አገልግሎት ባለሙያዎች፣ በፖሊስ፣ በባለጉዳዮቹና በህግ አስፈጻሚው አካላት መካከል አላስፈላጊ የሆነ አለመግባባትና አለመተማመን መፍጠርም ችሏል፡፡ የተደረጉት ውይይቶች ትኩረት ሰጥተው ያመላከቱት መሰረታዊ ጉዳይ የሚመለከታቸውን ሁሉንም አጋር አካላት የሚያስተሳስርና የእያንዳንዱን ሚናና ሀላፊነት በዝርዝር የሚያሳውቅ የጋራ የሆነ ሰነድ ተዘጋጅቶ መቅረብ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ይህ ደረጃውን የጠበቀ የአተገባበር ሥርአት ሰነድ ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት በሚያስችል ደረጃ የሚመለከታቸውን አካላትና አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ባለሙያዎችን በማካተት የተቀናጀና ሁሉን አቀፍ ሆኖ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

ዋነኛ ትኩረቱንም ወሲባዊ ጥቃት በደረሰባቸው ተጎጂዎች ላይ በማድረግ ተጎጂዎቹ ወንጀሉ ከተፈፀመባቸው ቦታ ከማህበረሰቡ ውስጥ ጀምረው ተገቢውን አገልግሎት ለማግኘት እንዲችሉ ለምሳሌ ወንጀለኛውን ለፍርድ እስከ ማቅረብና የመልሶ ማቋቋም አገልግሎት እስከሚያገኙበት ጣቢያ ድረስ ብሎም ወሲባዊ ጥቃትን እስከ መከላከልና ምላሽ እስከመስጠት ድረስ የሚያልፉባቸውን የተለያዩ ደረጃዎች እስከ መጨረሻው ጫፍ ድረስ በግልጽ ያመላክታል፡፡ በተጨማሪ ሰነዱ አነስተኛ የሆኑ መመሪያዎችን ጭምር በመዘርዘር ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የትኛው ተቋምና የማህበረሰብ አካል የትኛውን አይነት እርምጃ መውሰድ እንደሚገባው በአራቱ ዋነኛ ምላሽ ሰጪ አካላት ስር ማለትም በጤና፣ በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር/ማህበራዊና የስነልቦና፣ በህግ/ፍትህ፣ በፖሊስ/ደህንነት ስር ዘርዝሮ ያቀርባል፡፡

ይሄንን ደረጃውን የጠበቀ የአተገባበር ሥርአት ሰነድ ከብሄራዊና ዓለምዓቀፋዊ መመሪያዎች ጋር በማጣጣም ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በስልጠና ወቅት በማጣቀሻነት፤ አገልግሎት ሰጪ አካላትም በእለት ተለት እንቅስቃሴያቸው በመመሪያነት እንዲገለገሉበት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ሰነዱ በብሄራዊ አስተባባሪው አካል ሀላፊነት ስር ሆኖ የሁሉም አካላት ስምምነት በውስጡ ለሰፈሩት መመዘኛዎችና ተግባራት ተገዢ ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

# ክፍል-2

# ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ ወሰን እና የአገልግሎት ጣቢያ

## 2.1 ራዕይና ተልዕኮ

### ራዕይ

ሕብረተሰቡ ከማንኛውም አይነት ፆታዊ ጥቃት ነፃ ሆኖ ሴቶችና ሕጻናት ሰብአዊ መብታቸው ተከብሮ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነታቸው ተጠብቆና የሕይወት ምርጫቸው ተሟልቶ ማየት፡፡

### ተልዕኮ

ሁሉንም አይነት ወሲባዊ ጥቃቶችን በሁሉም ባለድርሻ አካላት የነቃ ተሳትፎ፣ የተቀናጀ አሰራርና ምላሽ በመከላከልና በማስወገድ የሴቶችንና የሕጻናትን መሰረታዊ መብቶች ማረጋገጥ፡፡

## 2.2 ዓላማ

### አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ሰነድ አጠቃላይ ዓለማ በብሄራዊ ደረጃ ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ብሎም ለማስወገድ፣ በየደረጃው ምቹ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ በብቃት መቅረቡን በማረጋገጥ ሁሉን አቀፍ በሆነ ስልት ሴቶችና ሕጻናት ተገቢውን የድጋፍ አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፡፡

### ዝርዝር ዓላማዎች

- በዚህ ሰነድ ዝግጅት ላይ የተሳተፉ ዋነኛ ባለድርሻ አካላት በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው የመለየት፣ አመራር የመስጠት፣ በመረጃ አያያዝ፣ ለወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች በቅብብሎሽ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት በሚያከናውኑበት ወቅት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአተገባበር ስርአቶችን ማሳወቅ
- የመልሶ ማቋቋም አገልግሎት ሰጪ አካላትን (በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ) አቅም በማጎልበት፣ የተቋማትን ተሳትፎ በመጠቀም የሚሰጠውን አገልግሎት ደረጃ በማሳደግና በማስፋፋት በደረሰባቸው ጥቃት ለተጎዱ ሴቶች ሁለገብ የሆነ የተቀናጀ ምላሽ መስጠት የሚያስችል ተቋማዊ የአሰራር ስልቶችን ማጎልበት
- ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች ሁለገብ የሆነ የስነልቦና፣ የህክምና፣ የማህበራዊና የህግ አገልግሎት ምላሽ መስጠት

- በመለየት፣ በድጋፍ መስጠትና በቅብብሎሽ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ባለሙያዎች፣ ተጠቃሚዎች፣ በየደረጃው የሚገኙ ሰራተኞች ስጋት የሆነውን የተጋላጭነት አደጋ በአስተማማኝ የሚስጥር አጠባበቅና ለደህንነት ጉዳዮች አስተማማኝ ከለላ ማድረግ

- ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ተጠቃሚውን ያማከለ ማለትም ተጠቃሚዋ/ ተጠቃሚው በሚሰጠው የአገልግሎት ሂደት ላይ ተሳታፊ እንድትሆን/እንዲሆን መርሆዎችን የተከተለ አገልግሎት መሰጠቱን ማረጋገጥ

- በወሲባዊ ጥቃት ዙሪያ ማህበረሰባዊ ግንዛቤን በማጎልበትና የማህበረሰብ ንቅናቄ በመፍጠር ማህበራዊ ለውጥ ማምጣት

## 2.3 የሰነዱ ወሰን

ይህ ሰነድ ማንኛውንም አይነት ህብረተሰቡን ለሚያውኩ ወሲባዊ ጥቃቶች ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ሀላፊነቶችን፣ ሚናዎችን፣ መርሆዎችንና መርህ ግብሮችን በዝርዝር ያሳውቃል፡፡ በወሲባዊ ጥቃት ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግና በተጨማሪም በሚያደርሳቸው የአካልና የስነልቦና ተጎጂዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ሰነዱ ተጎጂዋን ከቤተሰብ/ከማህበረሰብ ጀምሮ እስከ ጤና ተቋም፣ፖሊስ፣ የህግ አካላት፣ የማህበራዊና የስነልቦና ድጋፍ ሰጪዎች፣ የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ድረስ ያለውን እና ተመልሳ ትኖርበት ወደነበረው ማህበረሰብ ወይም ቤተሰብ እስክትመለስ ድረስ ያለውን አካሄድ ያሳያል፡፡ ሆኖም ግን ፆታ ላይ የተመሰረቱ በትምህርት ቤቶች የሚደርሱ ሌሎች ጥቃቶችን፣ ለፆታዊ ብዝበዛ የሚወሰዱትን፣ በመኖሪያ አካባቢ ከተዛባ የኢኮኖሚ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ፆታዊ ጥቃት፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለምሳሌ የሚስት ውርስ ወዘተ፣ የመሳሰሉትን በቀጥታ አያጠቃልልም፡፡ ሰነዱ ሁሉን አቀፍ የሆነ የመከላከልና ምላሽ መስጠት እንዲችል በየጊዜው የሚሻሻልና የሚስፋፋ ይሆናል፡፡ የቀረበ ሲሆን ተፈጻሚነቱ ግን በአጠቃላይ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች፣ ልጃገረዶች፣ ወንዶች ወይንም ታዳጊ ወንዶች ላይ የሚደርሰውን ሁሉ የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

**ማስታወሻ**፡- ይህ ሰነድ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በአነስታይ ጾታ (የእርሷ/እርሷ) በማለት የተገለጸው ቀለል ባለ ሁኔታ ተነባቢ እንዲሆን ታስቦ የቀረበ ሲሆን ተፈጻሚነቱ ግን በአጠቃላይ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች፣ ልጃገረዶች፣ ወንዶች ወይንም ታዳጋ ወንዶች ላይ የሚደርሰውን ሁሉ የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

## 2.4 የአገልግሎት ጣቢያዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች

ይህ በብሄራዊ ደረጃ የተዘጋጀ ሰነድ በየአካባቢው ለሚዘጋጁ ሰነዶች በመነሻነት እንዲያገለግል ታስቦ የአገሪቱን ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችንና ስርአቶችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ የሚዘጋጁት ሰነዶች የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት አድርገው የአገልግሎት ጣቢያዎች፣ የአደረጃጀት ሂደታቸው፣ ሀላፊነታቸው፣ ሚናቸውና የአሰራር ስርአቶችን ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡-

| የሚገኝበት ስፍራ | የአገልግሎት ጣቢያው አይነት | የሚመለከተው ባለሙያ | የሚተገበሩ ተግባራት |
|---|---|---|---|
| በማህበረሰብ | ጤና ኬላ፣ የመኖሪያ ቀበሌዎች፣ የማህበረሰብ ፖሊስ ጣቢያዎች ፣ የቀበሌ ሴቶች ተወካይ፣ የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ፣ የተለመዱ/ባህላዊ ሽንጎ | ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ፣ የጤና ልማት ሰራዊት ተወካይ፣ ህዝባዊ ፖሊስ፣ የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ፣ የአካባቢ ሽማግሌዎች፣ የህግና ማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት የህዝብ ተወካይ | ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ፣ የጤና ልማት ሰራዊት ተወካይ፣ ህዝባዊ ፖሊስ፣ የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ፣ የአካባቢ ሽማግሌዎች፣ የህግና ማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት የህዝብ ተወካይ |
| በዞን ደረጃ | ጤና ጣቢያ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች፣ ማህበራዊ የስነልቦና ድጋፍ ሰጪ አካል፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የአቃቤ ሕግ ጽ/ቤቶች፣ ፍርድ ቤቶችና የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ | የጤና ተቋም የወሲባዊ ጥቃት ተጠሪ፣ የስነልቦና ባለሙያ/የማህበራዊ ድጋፍ ሰራተኛ፣ የሰለጠነ የፖሊስ መኮንን፣ አቃቤ ሕግ፣ ጠበቃና የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ተወካይ | የግንኙነት ስርአት መዘርጋት፣ የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎችን መለየት፣ የህክምና ድጋፍ፣ ማህበራዊ የስነልቦና ድጋፍ መስጠት፣ ማስወገድ፣ መረጃዎችን ማሰባሰብና ማስቀመጥ፣ የአካባቢ ግጭቶችን ማስወገድ፣ የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአት መዘርጋት፣ መረጃዎችን መለዋወጥ፣ የፍርድ ቤት አካሄድ ስርአት ማሳወቅ |
| በክልል | ጠቃላይ/ልዩ ሆ/ል፣ ማህበራዊ የስነልቦና ድጋፍ፣ ክልላዊ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የአቃቢ ሕግ ቢሮዎች፣ ፍርድቤቶች፣ የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ | የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ/ የወሲባዊ ጥቃት ክሊኒኮች፣ የስነልቦና ባለሙያ/ የማህበራዊ ድጋፍ ሰራተኛ፣ የሰለጠነ የፖሊስ መኮንኖች፣ አቃቤ ሕጎች፣ የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ተወካይ | የግንኙነት ስርአት መዘርጋት፣ የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎችን መለየት፣ የህክምና ድጋፍ፣ መረጃዎችን ማሰባሰብና ማስቀመጥ፣ የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአት መዘርጋት፣ መረጃዎችን መለዋወጥ፣ የፍርድ ቤት አካሄድ ስርአት ማሳወቅ |
| በፌዴራል ደረጃ | ልዩ/ሪፈራልሆ/ታሎች፣.ጤ/ጥ/ ሚኒስቴር፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስትር፣ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን | የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተወካዮች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን | የግንኙነት ስርአት መዘርጋት፣ ብሄራዊ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣ ብሄራዊ መርሀግብር ማዘጋጀት፣ የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀት፣ የስልጠና መመሪያዎችንና ፖሮቶኮሎችን ማዘጋጀት፣ የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ መመስረት፣ ተግባራትን ማቀናጀት፣ መረጃዎችን መለዋወጥ፣ የክትትልና የግምገማ ስርአትን መመስረት |

## ክፍል-3
## ትርጉም፣ መርሆዎች፣ ሪፖርት አዘገጃጀት፣ የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአትና የድጋፍ ፈላጊዎች አካሄድ

### 3.1 የቁልፍ ቃላት ትርጉም

***ባለድርሻ አካላት (stakeholders)*** ፡- ጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ተሳታፊ የሆኑትን ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን፣ ድርጅቶችን፣ ተቋማትን ይመለከታል፡፡ ባለድርሻዎቹ ስደተኞችና የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች (ሁለቱ አካላት ባለድርሻ የሆኑበት ምክንያት የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ጾታዊ ጥቃት በስደተኞችና በተፈናቃዮች ላይ በብዛት የሚፈጸም መሆኑን ሲሆን ጥቃቱን በማጋለጥም ሆነ ጥቃቱ የደረሰባቸው ያልደረሰባቸውን በማስተማር ጥቃቱን ለመከላከልና ስርጭቱንም ለመቆጣጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ስለሚታመን ነው፡፡) በተጨማሪ የአካባቢ ሕብረተሰብ፣ ሰራተኞች፣ ፍቃደኛ የተባበሩት መንግስታት ተወካዮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት፣ እርዳታ ሰጪዎችና ሌሎች ዓለም አቀፍ የማህበረሰብ ባለድርሻ አካለት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪ የአካባቢ ሕብረተሰብ፣ ሰራተኞች፣ ፍቃደኛ የተባበሩት መንግስታት ተወካዮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት፣ እርዳታ ሰጪዎችና ሌሎች ዓለም አቀፍ የማህበረሰብ ባለድርሻ አካለት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

***አስተባባሪ አካላት (Coordinating agencies)*** ፡ወሲባዊ ጥቃት ላይ የሚሰራውን ቡድን የሚመራና የሚሰበስብ የመከላከልና ምላሽ የመስጠት አገልግሎት ከዝቅተኛው ደረጃ ጀምሮ በቦታው መሰጠቱን የሚያረጋግጡ ድርጅቶችን ይመለከታል፡፡

***ሥርዓተ ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት (Gender based Violence)*** ፡ቅል የሆነ ሀረግ ሲሆን ማንኛውም አይነት ከሰው ፍላጎት ውጪ የሚፈጸምን ጎጂ ድርጊት ያመለክታል፡፡ መንስኤው ማህበረሰቡ በወንዶችና በሴቶች መካከል በፈጠረው የሥርዓተ ፆታ ልዩነት ላይ የተመሰረተን ድርጊት ያጠቃልላል፡፡

***ወሲባዊ ጥቃት (Sexua Violence)*** - ማንኛውንም አይነት ጥቃት፣ ወሲብ ለመፈጸም የሚደረግ ሙከራ፣ ያልተፈለገ ፆታዊ ትችት ወይንም አድናቆት፣ ወይንም ለወሲባዊ ፍላጎት ሲባል ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሙከራ፣ በማስገደድ፣ ጉዳት በማድረስ፣ በማስፈራራት፣ ወይም ጉልበትን በመጠቀም በማንኛውም ሰው ላይ ከተጠቂው ሰው ጋር ያለው ግንኙነት ምንም ይሁን ምንም፣ በየትኛውም ቦታ በመኖሪያ ቤትም ሆነ በስራ ቦታ፤ ስፍራ ሳይመርጥ የሚፈጸም ጥቃት ማለት ነው፡፡ ፆታዊ ጥቃት የተለያዩ ገጽታዎች ያሉት ሲሆን አስገድዶ መድፈርን፣ ፆታዊ ባርነት (ግዞት) ወይንም ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ፣ በማስገደድ የተፈጸመ እርግዝናን፣ ፆታዊ ማስጨነቅ (ማሸማቀቅ)፣ ወሲባዊ ብዝበዛና ጉዳት በማስገደድ የሚፈጸምን የፅንስ ማስወረድን ያጠቃልላል፡፡

1. **አስገድዶ መድፈር (Rape)**፡-ያለምንም ስምምነት በሴቷ የመራቢያ አካል፣ በፊንጢጣ ወይንም በአፍ ባእድ አካል ወይንም የሰውነትን አካል መጨመር ማለት ነው፡፡
2. **ፆታዊ ጥቃት (Sexua assault)**፡- ማንኛውም አይነት የማይፈለግ ፆታዊ ንክኪ ማለት ሆኖ የውጭ አካልን ወደ ሰው የውስጥ አካል መጨመርን የማያካትት ማለት ነው፡፡

**3 አካላዊ ጥቃት (Physica assault)፡-** ያታዊ ግንኙነትን የሚያካትት ሆኖ በአካል ላይ የሚፈጸም ድብደባ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በዱላ መምታት፣ በጥፊ መምታት፣ መቁረጥ፣ መግፋት፣ የአካላዊ ቅጣት የሚያስከትል ወንጀል (ለሞት የማያበቃ) ፣ ወዘተ.

**4 ስነልቦናዊ ጉዳት(Psychologica abuse)፡-** አላስፈላጊ የስም መጥራት፣ እደባድባለሁ ብሎ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ማንጓጠጥ፣ አስገድዶ መለየት (ይሄም አንድን ሰው ከቤተሰቡ ወይንም ከጓደኞቹ መለየት) ይመለከታል፡፡ ይሄ ምድብ በሚከተለው መልኩ ትርጉም የተሰጣቸውን ሁሉንም አይነት ፆታዊ ማሸማቀቅ ያጠቃልላል፡- የማይፈለግ ትኩረት፣ መለየት፣ አካላዊ ምልክት መስጠት ወይንም የተጻፉ ወሲባዊ ቃላትን ወይንም ዛቻ የተቀላቀለባቸውን (አካላዊ ግንኙነት ሳይኖር) የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

**5 ኢኮኖሚያዊ ጉዳት (Economic abuse)፡-** ገንዘብ ወይንም የቤት ቁሳቁሶችን አብሮ በሚኖር ሰው ወይንም በቤተሰብ አባል መከልከል (በቤተሰብ ደህንነት ላይ ጉዳት በማድረስ) ለኑሮ የሚደረግን ጥረት በመከታተል (ባሏ የሞተባትን ሴት የውርስ መብቷን መከልከል) የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ ይሄ ሁኔታ በአጠቃላይ ከድህነት ጋር ተያይዞ የሚመጣ ጉዳትን/አለመግባባትን አያጠቃልልም፡፡

**6 በማስገደድ የተፈፀመ ጋብቻ (Forced marriage)፡-** ግለሰቦችን ከፍቃደኝነታቸው ውጪ ጋብቻን መፈፀም፡፡ (ያለእድሜ ጋብቻን ያጠቃልላል)

**7 የሴቶች ግርዛት/መቆረጥ(Female genita mutilation/cutting)፡-** ጤናማ የመራቢያ አካልን መቁረጥ

**8 የህፃናት ወሲባዊ ጥቃት (Child sexua abuse)፡-** አ አንድ ህፃን እሷም ሆነች እሱ ምን እየተደረገ እንደሆነ በሚገባ በማይረዱበት ሁኔታ ፣ ተነጋግሮ ስምምነት ማድረግ በማይችሉበት ሁኔታ፣ ወይንም የህፃኑን እድገት ወሲባዊ ግንኙነት ለማድረግ ባልጎለበተበት ሁኔታ፣ ወይንም በህግ የተደነገገውን በሚያዛባ ሁኔታ ወይንም የማህበረሰቡን ወግና ስርአት በሚያዛባ ሁኔታ የሚፈጸም ማለት ነው፡፡

**9 ተጎጂ/ጥቃት የደረሰበት/ባት ሰው (Surviver/victim)፡-** ወሲባዊ ጥቃት የደረሰበት(ባት) ሰው ማለት ነው፡፡ ተጎጂ ወይንም ጥቃት የደረሰበት የሚሉት ቃላቶችን በማቀያየር ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ጥቃት የደረሰበት(ባት)የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ በህግ አካላትና በህክምና ባለሙያዎች ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን ተጎጂ የሚለው ቃል ግን በስነልቦናና በማህበረሰባዊ አገልግሎት አካላት በአጠቃላይ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን ተመልሶ የማገገም ሁኔታን ያመለክታል፡፡

**10 ወንጀለኛ (Perpetrator)፡-** አንድ ሰው ወይንም ቡድን ወይንም ተቋም በሌላ ሰው ላይ ከሷ ወይም ከሱ ፍቃደኝነት ውጪ በቀጥታ ወንጀል የሚፈጽም ወይንም ጥቃት እንዲፈጸም የሚተባበር ወይም ጉዳት እንዲደርስ የሚያደርግ ማለት ነው፡፡

**11 ዳግም ጥቃት (Secondary victimization)፡-** በቀጥታ በጥቃቱ የሚደርሰውን ጉዳት የሚመለከት ሳይሆን ለተጎጂዋ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወይንም በግለሰቦች ምላሽ አሰጣጥ ችግር ምክንያት የሚደርስ ጥቃት ነው፡፡

**12 መልሶ ማቋቋም (Rehabilitation)፡-** ያሉትን ስልቶች፣ ዘዴዎችና ስትራተጂዎች በማዋሀድ የተጠቂዎችን አቅም በማጎልበት ችግራውን መቋቋም እንዲችሉ አቅም የፈቀደውን ሁሉ ጥረት በማድረግ ስነልቦናዊ፣ ስሜታዊ፣ አካላዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን ተቋቁመው የተሻለ ሕይወት እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡

**13 ባለሙያ/ሰራተኛ (Professional/Personnel)፡-** ከስራቸው ጋር በተያያዘ ከተጠቂዎች ጋር ተገናኝተው ለችግራቸው መፍትሄ የመስጠት ሀላፊነት ያለባቸው ሰዎች ማለት ነው፡፡

**14 "ተጎጂ ህፃናት"/ጥቃት የደረሰበት/ባት ህፃን (Child Victim)፡-** እድሜው ከ18 አመት በታች የሆነች/ነ ጥቃት የደረሰባት/በት ሰው ማለት ሲሆን እሷ ወይም እሱ ለደረሰው ጥፋት አስተዋጽኦ ቢኖራትም ባይኖራትም ወይንም በሕግ አስከባሪ (አቃቤ ሕግ) ጥፋተኛ የተባለች ወይንም ጥፋተኛ የተባሉ ህፃናትን ያጠቃልላል፡፡

15 **"አገናኝ" (Intermediary)**፡-የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ሆኖ በፍርድ ቤት በተያዘው ጉዳይ በህፃኑና በፍርድ ቤት መካከል ግንኙነት የሚፈጥር

16 **የወንጀል ፍርድ አፈጻጸም"(Crimina ustice process)**፡- በደረሰው ጥፋት ላይ የተበየነውን የካሳ አግባብነት ማረጋገጥ፣ በምርመራው ላይ የቀረበውን ቅሬታ ተቀብሎ ማስተናገድ፣ አቃቤ ሕጉን፣ ፍርዱን እና ከፍርዱ በኋላ ያለውን ሁኔታ በአጠቃላይ ሂደቱን መከታተልን ያጠቃልላል፡፡

17 **"ለሕፃናት ምቹና ተስማሚ/ጥንቃቄ የተሞላበት (Child Friendly/Sensitive)**፡-በመጀመሪያ የሕፃናት መብት መጠበቁን ታሳቢ የሚያደርግ ሲሆን የሕጻናን ፍላጎትና አስተያየት ከግምት ውስጥ ያገባ አቀራረብ/አያያዝ ነው፡፡

18 **"ድጋፍ ሰጪ" (Support Person)**፡- በልዩ ሁኔታ ሰልጥኖ አንድን ህፃን በአጠቃላይ በፍርድ ሂደቱ ውስጥ የማስገደድ/የማስጨነቅ ስጋትና በድጋሚ ጥቃት ላይ እንዳትወድቅ ወይንም ለዳግም ጥቃት እንዳትጋለጥ ድጋፍ የሚሰጥ ሰራተኛ ማለት ሲሆን በማቆያ ቤት ውስጥ የሚሰሩ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

19 **ተንከባካቢ (Guardian)**፡- ቤተ-ዘመድ ወይንም ለአንድ ህፃን እንክብካቤ እንዲያደርግ በሕግ እውቅና የተሰጠው ሰው፡፡

## 3.2 መርሆዎች

ሁሉም ባለድርሻ አካላት ያለምንም ልዩነት በተስማሙት መሰረት ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባት ተጎጂ የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ሲሰጡ ባህሪያቸውንና አሰራራቸውን ለሚከተሉት መርሆዎች ተገዢና ታማኝ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ለሰራተኞቻቸው ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ እንደሚያደርጉና በተጠያቂነት መንፈስ መርሆዎቹን በሚገባ በመተግበር ሀላፊነታቸውን ይወጣሉ፡፡

### አጠቃላይ መርሆዎች፡-

- በኢትዮጵያ ህገመንግስት፣ በክልሎችና በአለም አቀፍ ሰነዶች ላይ የሰፈረውን የሰብአዊ መብት መርሆዎች በመከተል በቁርጠኝነት መተግበር፡፡
- የህፃናትን በተለይ የልጃገረዶችን ልዩ ፍላጎት ማስከበር
- በሴቶች ላይ የሚደርስን ጥቃት ለመከላከል የማህበረሰቡን አቅም በማጎልበት፣ በንድፈ-ሀሳብ ዝግጅት፣ አተገባበርና የግምገማ ስርአት ላይ አሳታፊ የሆነ አሰራር መዘርጋት
- በግልጽ ተለይቶ በታወቀ ሀላፊነትና የተጠያቂነት አሰራር፣ በመረጃ የተደገፈ፣ በእውቀት ሽግግርና በክህሎት ግንባታ ሁሉን አቀፍ የሆነ አጋርነትንና ሕብረትን መፍጠር

### የአገልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች

- የተጎጂዎችን ደህንነት፣ ከአካላዊ ጉዳት ተጠብቀው፣ ለኢኮኖሚያዊ ችግር ሳይጋለጡ፣ ጥቃቱን ሊያደርስባቸው የሚችለውን የተወሳሰቡ ችግሮች ተቋቁመው የተቃና ህይወት መኖር እንዲጀምሩ ማገዝ
- ተጎጂዎች ተገቢውን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ በደረሰባቸው ጥቃት የተነሳ ሊደርስባቸው የሚችሉ መገለሎችን ታሳቢ በማድረግ የተወሰነ የድጋፍ አማራጮች እንደሚደረግላቸው ማረጋገጥ

- አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች የሰለጠኑ፣ ለሥርዓተ ፆታ እኩልነት ከበሬታ ያላቸው፣ ተከታታይ የሆነ ስልጠና ያገኙ፣ ስራዎቻቸውን ግልጽ በሆነ መመሪያ ፣ ፕሮቶኮል፣ በሙያ ስነምግባር ላይ ተመስርተው እንደሚያከናውኑ፣ አስፈላጊ በሆነበትም ቦታ አገልግሎቱ በሴት ሰራተኞች ሊሰጥ እንደሚችል ማረጋገጥ
- የተጎጂዎች የግል ሚስጥር በሚገባ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ
- በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚደርሰውን ወሲባዊ ጥቃት መከላከል
- ለወሲባዊ ጥቃት ተጋላጭ ለሆኑና ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች ሌሎች ተጨማሪ አገልግሎቶች የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ ማስተባበርና ማቀናጀት
- የተሰጡ አገልግሎቶችን መገምገም
- ተጎጂዎችን የሚወነጅሉ (ተጠያቂ የሚያደርጉ) አመለካከቶችንና አስተሳሰቦችን ማስወገድ
- ሴቶች የራሳቸውን ሕይወት መቆጣጠርና መምራት እንዲችሉ አቅማቸውን ማጎልበት
- የሕክምና አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ለተጎጂዎች የሚሰጠው አገልግሎት በጤና አገልግሎት ስርአቱ ውስጥ እንዲካተት የሚያስችል የስልጠና ፕሮቶኮል በማዘጋጀት የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአቱ የጤና አገልግሎት በሚሰጡ፣ በምክክር አገልግሎት በሚሰጡ፣ በቤት ውሰጥ፣ በወንጀል ፈጻሚዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ በሚያስፈጽሙና በፕሮግራም ሀላፊዎች መካከል ተግባሪዊ እንዲሆን ማድረግ፡፡

## ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከል መርሆዎች

- በሁሉም ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚደርስን ጥቃት ለመከላከል ቅድሚያ መስጠት
- በሁሉም ክፍሎች ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከል የሚውልን የተወሰነ ግብአት መመደብ
- በሴቶችና ህፃናት ላይ የጥቃት መንስኤ የሚሆኑትን በተለይ ከሥርዓተ ፆታ ጋር በተለምዶ የተያያዙትን መንስኤዎች ለማስወገድ የሚረዳ የመከላከል ስልት (ስትራቴጂ) ማዘጋጀት
- ምን አይነት የመከላከል ስልት(ስትራቴጂ)? እና እንዴት? የሚለውን የሚያብራራ የክትትልና የግምገማ ሂደትን ያካተተ ግልጽ የሆነ ዝርዝር የአሰራር ስርአት ማዘጋጀት
- የመከላከል ስልት(ስትራቴጂ) በሚዘጋጅበት ወቅት የሴቶችን ድምጽ እና ቀጣይ ፍላጎት በተለይ ተጎጂ ሴቶችንና ህፃናትን ያማከለ መሆኑን ማረጋገጥ
- ሁሉንም ጉዳዮች ያካተተና ውጤታማ ስልት(ስትራተጂ) ለማዘጋጀት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ብሎም ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከሰራተኞችና ከአሰሪ ማህበራት፣ ከማህበረሰብ መሪዎች ጋር የተቀናጀ ስራ መስራት
- ወንዶች በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚያደርሱትን ጥቃት ለመከላከል በስትራተጂ ዝግጅትና አተገባበር ላይ ወንዶችና ወጣት ወንዶች በአጋርነት እንዲሰለፉ ማሳተፍ
- የሴቶችንና ህፃናትን ደህንነት አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ ከባቢያዊ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ ለውጥ በማምጣት ጭምር ማስፋፋት
- የመከላከል ጥረት ሁሉን አቀፍ መሆኑን በርካታ የመድሎ አይነቶችንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ቁልፍ ጉዳዮች ለምሳሌ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አካቶ መሆን እንደሚገባው ማረጋገጥ

- የማህበረሰብ የደህንነት ቁጥጥር (ኦዲት)በማካሄድ አደገኛ የሆኑ ቦታዎችን መለየት፣ በሴቶች ስጋት ላይ ውይይት በማድረግ ለድህንነታቸው መሻሻል የሚረዱ አስተያየቶቻቸውን መሰባሰብ፡፡

## የሁሉም አርምጃዎች መሪ መርሆዎች

- ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት በእያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት መካከል የተሟላ ትብብርና መደጋገፍን ማስፋፋት፡፡ በሁኔታዎች ላይ የተሰሩ ትንታኔዎችንና በዳሰሳ ጥናት የተገኙ መረጃዎችን በማካፈል ድግግሞሽን በማስወገድ የጋራ የሆነ መረዳትን ማጎልበት ያስችላል፡፡
- ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በአካላት መካከልና በውስጣዊ የድርጅቶች አደረጃጀት መሀል የህብረት አሰራርን በቀጣይነት ማረጋገጥ
- የሴቶችን፣ ህፃናትንና የልጃገረዶችን መብት ለማክበርና ለማስጠበቅ ህብረተሰቡን በሙሉ በሥርዓተ ፆታ እኩልነትና በሀይል አሰላለፍ ላይ ግንዛቤውን ለማጎልበትና ለማስፋፋት ተሳታፊ ማድረግ፡፡
- ሴቶችን/ወንዶችንና ልጃገረዶችን/ወጣት ወንዶችን በዳሰሳ ጥናት፣ እቅድ በማዘጋጀት፣ በአተገባበር፣ ፕሮግራሞችን በመከታተልና በመገምገም እኩልና ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያበረክቱ ማበረታታት፡፡
- ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከል አሰራር በሁሉም ፕሮግራሞችና አካላት ጋር ማቀናጀትና መዘርጋት
- በሁሉም ደረጃዎች የተጠያቂነትን አሰራር ማረጋገጥ

## ከግለሰብ ተጎጂዎች ጋር የመስራት መርሆዎች

- ምንጊዜም የተጎጂዋንና የቤተሰቦቿን ደህንነት ማረጋገጥ
- ምንጊዜም የተጎጂዋን(ዎችን) እና የቤተሰቦቻቸውን የግል ሚስጥር መጠበቅ ማክበር
- ተጎጂዋ ስምምነቷን ከሰጠች ወይም ከገለፀች ለሌሎች መሰጠት ያለበት መረጃ ተጎጂዋን ለመርዳት የሚያስችል ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ በቀብብሎሽ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት ተጠቃሚ ለማድረግ፡፡
- ስለተጎጂዎች በፅሁፍ የተያዙ ሁሉም አይነት መረጃዎች አስተማማኝ በሆነ ሚስጥራዊ አያያዝ በሚቆለፍ የፋይል ካቢኔት ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡
- የተጎጂዎችን ፍላጎት፣ ምርጫ፣ መብቶችና ክብር ማክበር
- በተጎጂዎች ላይ ምንም አይነት መድሎና ልዩነት ሳይደርስባቸው ሁሉንም አይነት አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ማረጋገጥ መርሆዎቹ ከተጎጂ ሕጻናት ጋር በሚሰራበት ጊዜ የሚተገበሩ ይሆናሉ፡፡ ሕጻናት ከሙብታቸው ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ የመሳተፍ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከላይ የተዘረዘሩት መርሆዎች በሙሉ ሊከበሩላቸው ይገባል፡፡ በህፃኗ ቦታ በመሆን ቤተዘመዶቿ ወይንም ጠባቂዎቿ/ሞግዚቷ ውሳኔ ከተሰጠ የህፃኗ ጥቅምና ደህንነትን ቀዳሚ በማድረግ ተገቢው የአሰራር ደረጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ / የዓለም ጤና ድርጅት የስነምግባርና የደህንነት ሰነዶች በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የተወሰኑ መመሪያዎችን የሚያቀርብ ሲሆን ተጨማሪ የመረጃ ምንጮችም ቀርበዋል፡፡/

## 3.3 ሪፖርት ማድረግና የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአት

በሁሉም ቦታ ግልጽ የሆነ የሪፖርት አደራረግና የቅብብሎሽ አገልግሎት ስርአት በመመስረት የተጎጂዎች ምስክሮች በአጋጣሚው ላይ ለማን ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸውና ምን አይነት ድጋፍ ከጤና፣ ከህግ፣ ከማህበራዊ ደህንነት፣ ከደህንነት ሀይሎችና ከሌሎች አካላት ማግኘት እንደሚጠብቁ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

ተጎጂዎች አብዛኛውን ጊዜ የደረሰባቸውን ጉዳት በተመለከተ እርዳታና ሪፖርት ለማድረግ የሚመጡት ምቹ፣ ሚስጥራዊነቱ፣ ተደራሽነቱና ተአማኒነቱ የተጠበቀ ነው ብለው ወደሚያምኑት ቦታ ነው፡፡ ሴቶቹንና ልጃገረዶቹን ይሄ ቦታ የት ሊሆን እንደሚችል መጠየቅ፡፡ ከማህበረሰቡ ለወሲባዊ ጥቃት ምላሽ ለመስጠት ምቹ የሆነው ቦታ የት እና ከየትኛው ድርጅት(ቶች) ጋር ሊሆን እንደሚገባው አስተያየታቸውን መጠየቅ፡፡ የመጀመሪያውን መነሻ ነጥብና ቀላል መረጃዎችን እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርጉና የቅብብሎሽ አሰራሮችን በስእላዊ መግለጫና
በአካባቢው ቋንቋ በማዘጋጀት በህብረተሰቡ ውስጥ በማሰራጨት የተቻለውን ያህል ብዙ ሰዎች እርዳታ ለማግኘት የት መሄድ እንዳለባቸውና ምን እንደሚጠብቁ ግንዛቤ መፍጠር፡፡

### በኢትዮጵያ አስፈላጊ የሆነ የሪፖርት አቀራረብ

በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ማንኛውም አይነት በሕጻናት ላይ የተፈጸመ ወሲባዊ ጥቃት በአፋጣኝ ለፖሊስ ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በእንደዚህ አይነቶቹ ጥቃቶች ላይ የሪፖርት አደራረግ መስፈርቶች የጤና አገልግሎት ሰጪዎችንና ሌሎች አካላት መሪ ከሆነው መርሆ ጋር በሚፈጥሩት ከፍተኛ ግጭት፤ በሚስጥር አጠባበቅ፣ ለነጻነት በሚገባው ከበሬታና ለተጋላጮች ሊሰጥ ስለሚገባው ጥበቃ ግራ መጋባት ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን በድጋሚ የወጣው ሕግ ማንኛውም ሰው የጤና አገልግሎት ባለሙያዎችንም ጨምሮ የወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን በተለይ በህፃናት ላይ የሚፈጸሙትን ሪፖርት የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

*የወንጀል ህግ አንቀፅ 443-ወንጀልን አለማሳወቅ* ሀ) ማንኛው ሰው በቂ ምክንያት ሳይኖረው *በሞት ወይንም በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል መፈፀሙን*ወይንም*ሞት ወይንም በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል መፈፀሙ*
የወንጀለኛውን ማንነት እያወቀ ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ በሕግ ወይንም በሙያው ደንቦች ደህንነት ወይም ሰላምና ሥርአት ሲባል አንዳንድ ወንጀሎችን ወይንም አንዳንድ ከባድ ሁኔታዎችን ለሚመለከታቸው ባለስልጣኖች የማሳወቅ ግዴታ እያለበት ይህን ግዴታውን ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ከብር አንድ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ወይንም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

*በአንቀፅ 835- የማሳወቅ ግዴታ አለመፈጸም*

በሕግ አንዳንድ ጉዳዮችን የማሳወቅ ግዴታ ኖሮባቸው በተለይም የተላላፊ በሽታ፣ የዕፅ ሱሰኝነት፣ የእንስሳት ባህሪ *የወንጀል ባህሪ ያላቸው* ወይም በሕብረተሰቡ በጠቅላላው አደገኛ የሆኑ ድርጊቶች መዛመቱን ወይንም ስርጭቱን ለመከላከል የሚጠቅሙ ጉዳዮችን አግባብ ላለው ባለስልጣን ያላሳወቁ ሃኪሞች፣ የጥርስ ሃኪሞች፣ መድሀኒት ቀማሚዎች፣ አዋላጆች፣ የእንስሳት ሃኪሞች፣ እንዲሁም በሽተኞችን እንዲያስታምሙ በአግባቡ የተፈቀደላቸው ሰዎች ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ነገሩ ከበድ ያለ እንደሆነ ወይንም በተደጋጋሚ ጊዜ በማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣሉ፡፡

የተከሰተውን ወንጀል የፈጸመው ዘመድ ወይንም የቤተሰብ አባል ከሆነ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባት ልጅ ተከታታይ ለሆነ ወሲባዊ ጥቃት የመጋለጥ እድል ሊገጥማት እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ ለፖሊስ በማመልከት ጥበቃ ሊደረግላት ይገባል፡፡ ሁሉም የጉዳዩ ተዋናዮችና የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ምንጊዜም የፖሊስና ለተጎጂዋ አገልግሎት ለመስጠት ሀላፊነት የተሰጣቸውን አካላት ስልክ ቁጥርና አድራሻ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ስለደረሰው ጉዳት በመገናኛ ብዙሀን ለህዝብ ማሳወቅ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ መቅረብ ያለበት በድምጽና በጽሁፍ በተጎጂው ወይንም በጠባቂው(ባሳዳጊው) ፍቃደኝነት/ስምምነት ከተደረሰ በኋላ መሆን ይኖርበታል፡፡ (በተጨማሪ ጠባቂው/ተንከባካቢው ጥቃቱን ያደረሰው ሰው አለመሆኑ ወይንም የጥቃቱ ተባባሪዎች አለመሆናቸውን መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ድርጅቱ ከመገናኛ ብዙሀን ጋር ግንኙነት የሚያደርግና መግለጫ የሚሰጥ አንድ ሰራተኛ በተጠሪነት መመደብ ይኖርበታል፡፡

ሆኖም ግን ተጎጂዋ በምንም አይነት መልኩ የተሳታፊውን/ዎቹን፣ ድጋፍ ሰጪውን/ዎቹን፣ እና/ወይንም የአገልግሎት ሰጪው ድርጅት/ቶችን ማንነትና ፍላጎት ለማስተዋወቅ/ለማራመድ መዋል አይኖርበትም፡፡ የተጎጂዋን ማንነት ለእንደዚህ አይነት ደርጊት ማዋል እንደ ብዝበዛ ስለሚቆጠር በምንም አይነት መፈጸም አይኖርበትም፡፡ የተጎጂዋን(ውን) ታሪክ ወይንም ምስል ማሰራጨት መለያን በመቀየርም ሆነ ማንነትን በመሸፈን ተጎጂዋን፣ ወንድሞችን/እህቶችን ወይንም ጓደኞችን ስጋት ላይ ሊጥላቸው ስለሚችል መፈጸም አይኖርበትም፡፡ መገናኛ ብዙሀን ተጨማሪ ስቲግማ(መገለል) በማንኛውም ተጎጂ ላይ እንዳይፈጥሩ በማረጋገጥ ተጠቂዎችን መቦደን ወይንም መለያ ስም/ምልክት መስጠት ወደ እማይፈለግ የአፀፋ ምላሽ በተጨማሪም ለተጨማሪ የአካል ወይንም የስነልቦና ጉዳት ወይንም ለእድሜ ልክ ጉዳት፣ መገለል ወይንም በሚኖሩበት አካባቢ ባለው ሕብረተሰብ የመገለል አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

# ክፍል-4
# ለወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች የምላሽ ሰጪ አካላት የአሰራር ሂደት

## 4.1. አጠቃላይ የአካላት ምላሽ አሰጣጥ

### የመጀመሪያ ቦታ

ተጎጂዋ የደረሰባትን የወሲባዊ ጥቃት ገጠመኝ ለመረጠችው ማንኛውም ሰው/አካል ሪፖርት የማድረግ መብት አላት፡፡ ተጎጂዋ ሪፖርት የምታደርግበት የመጀመሪያው ቦታ ከሚከተሉት ውስጥ ለአንደኛው ሊሆን ይችላል፡-

- ለወላጆቿ ወይንም ለቤተሰቦቿ
- ለትምህርት ቤት መምህራን፣ ለአቻዎቿ እና ለጓደኞቿ
- ለሴቶች የልማት ቡድን
- ለጤና ባለሙያዎች
- ለሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር/ቢሮ/ጽ/ቤት ተወካይ
- ለሕግ ድጋፍ ሰጪዎች
- በከተማ ወይንም በቢሯቸው ውስጥ ለሚገኙ የፖሊስ ወይንም የደህንነት አባላት
- ተጎጂዋ ድጋፍ ያደርግልኛል ብላ ላመነችው ማንኛውም ሰው

ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባት ድጋፍ ለማግኘት የቀረበቻቸው ሁሉም ባለድርሻ አካላት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ አገልግሎቶችንና አጠቃላይ መረጃዎችን ለተጎጂዋ የማሳወቅና ጉዳቱን ሪፖርት የማድረግ ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ባለድርሻ አካላቱ ተጎጂዋን በቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጡ ስርአት መሰረት ደረጃውን ጠብቆና በዛ ደረጃ ያለው አካል የሚሰጠውን የጤና፣ የስነልቦናና የህግ አገልግሎት ታሳቢ በማድረግ መላክ ይኖርበታል፡፡

### የስምምነትና የመረጃ ልውውጥ

በወሲባዊ ጥቃት ላይ የሚሰጡ መረጃዎች ጥብቅ የሆነ ጥንቃቄ የሚፈልጉና አስተማማኝ የሆነ የሚስጥር ጥበቃን የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ማንኛውንም አይነት ከወሲባዊ ጥቃት ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎችን አሳልፎ መስጠት እጅግ አስጊ የሆነ በቀጣይም የተጊጂዋን ህይወትና የሚረዷትንም ሰዎች ስጋት ላይ የሚጥል ነው፡፡ የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች በግል ጉዳያቸው ላይ ለተቋማትም ሆነ ለግለሰቦች መረጃዎቻቸው እንዴት እንደሚሰጡ የመቆጣጠር መብት አላቸው፡፡ ባለጉዳዩ መረጃዎችን ለሌላ አካል ማካፈል ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ተረድቶ መረጃው ከመሰጠቱ በፊት ተገቢው ውሳኔ ላይ መድረስ ይኖርበታል፡፡ ተጎጂዋ ተስማምታ ወደሚቀጥለው አገልግሎት ለመሄድ ጥያቄ ካቀረበች ምንም አይነት መረጃ ለሌላው አካል ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን መረጃ እንድታገኝ ተደርጎ ፍቃድ መስጠት ይኖርባታል፡፡ ስላለችበት ሁኔታ ማንኛውንም አይነት መረጃ ለሌላ አካል መስጠት የሚፈጥረውን ስጋትና ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በቅድሚያ በሚገባ ማስገንዘብ ይገባል፡፡ ተጎጂዋ ለሌላ አካል የሚተላለፉ የመረጃ አይነቶች ላይ ገደብ የማድረግና ለየትኛው ድርጅት እንደሚሰጥ ለየትኛው እንደማይሰጥ የመወሰን መብት አላት/ቸው፡፡ ተጎጂዋ ቃለመጠይቅ ለማድረግ፣ አካላዊ ምርመራ ለማድረግ፣ የላቦራቶሪ ምርመራ ለማድረግ፣ ለፍርድ ሂደቱ የሚረዱ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ያልተገኙ መረጃዎችን ለዳታ ስብስብ ጥቅም ለማዋል ለማካፈል በቅድሚያ ተረጂዋ ፍቃዷን መስጠት ይኖርበታል፡፡

ሕጻናትን በመረዳት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ፍቅር በተሞላበት የህፃናት አያያዝ ዘዴ በመጠቀም እራሳቸውን መግለጥ እንዲችሉ ለማበረታታት የምክክር አገልግሎትና ሁሉንም አይነት ጠቀሜታ ያላቸውን መረጃዎች ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ህፃናት በሚሰጡት መረጃ ጠቀሜታና ተአማኒነት ላይ ለመወሰን ሕጻናቱ ያላቸው አቅም በእድሚያቸው ደረጃ፣ በአዕምሯቸው ብስለት፣ እራሳቸውን በነጻነት ለመግለጽ ባላቸው ችሎታ ላይ የሚወሰን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ማንኛውም ሰው እድሜው ከ18 አመት በታች ከሆነ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ/እንደ ህጻን ስለሚታይ በሕጻኑ ቦታ ዘመዶች ወይም ህጋዊ እውቅና ያለው አሳዳጊ/ ሞግዚት በፍቃድ መስጫ ሰነዱ ላይ እንዲፈርም ይደረጋል፡፡ ቤተዘመድ ወይንም አሳዳጊ/ሞግዚት ከሌላት ጥበቃ እያደረገላት ያለው ፖሊስ የፍቃድ መስጫ ሰነዱን ይፈርማል፡፡ ምንም አይነት ሰው በማይኖርበት ሁኔታ የህክምና ባለሙያው የመግባቢያ ሰነዱን እንዲፈርም ተደርጎ አስፈላጊው አሰራር ይቀጥላል፡፡ ወሲባዊ ጥቃቱ በሕጻኑ ላይ ያደረሰው ጉዳት አስከፊ በሚሆንበት አጋጣሚ ሁኔታው ለአስፈላጊው መንግስታዊ አካል ሪፖርት በማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ጠቃሚ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ የመግባቢያ ቅፁን በእዝል-1 መሰረት ይጠቀሙ፡፡

## ግብአት/ የመነሻ ጥናት

ተጎጂዋ በአካሏ፣ በስነልቦናዋና በማህበራዊ ኑሮዋ ላይ በደረሰው ጉዳት ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት መካሄድ የሚኖርበት ምን አይነት አካላዊ ህክምና፣ የስነልቦና ህክምና ወይንም ማህበራዊ አገልግሎት እንደሚያስፈልጋት ለመወሰንና የተጎጂዋን ህይወት ከአደጋ ለመከላከል ታስቦ መሆን ይኖርበታል፡፡ ቅደም ተከተሉ በቅድሚያ ከተጎጂዋ ጋር ግንኙነት ያደረገውን ድጋፍ ሰጪ አካል ሙያ ይጠይቃል፡፡ የግለ ታሪክ አመራር ቡድን ወይንም የባለሙያዎች (የሚገኝ ከሆነ) ስብስብ ቢሆን ምቹ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ምርመራው በተጎጂዋና በቤተሰቧ ላይ የሚደርሱ በርካታ ገጽታ ያላቸው ተጽእኖዎችን ሊዳስስ የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ ይሄንን ሰነድ የሚጠቀሙ አካላት ትኩረት ማድረግ የሚገባቸው በአብዛኛው ግለ-ታሪክ ምርመራ የማይኖር በመሆኑ ማንኛውንም በእጃቸው የሚገኘውን የመረጃ ምንጭ ጥቅም ላይ ለማዋል ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የተለያየ የሙያ ባለቤት የሆኑ የባለሙያዎች ስብስብ ለማህበረሰባዊ የስነልቦና መልሶ ማቋቋም አገልግሎት ሊኖራቸው የሚችለውን ጠቀሜታ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ የተለያዩ የሙያ ባለቤት ባለሙያዎች ስብስብ ግዴታ የአንድ ተቋም ቅጥር መሆን አይኖርባቸውም፡፡ ሌሎች አማራጮች ለምሳሌ የተወሰኑ ባለሙያዎችን በጊዜያዊነት በመቅጠር ወይንም የሌላ ድርጅት ባለሙያዎችን የግንኙነት መረቡን በመጠቀም ሊሰራ እንደሚችል ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የቡድኑ አባላት የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች፣ ሳይኮሎጂስቶች፣ የስነ-አዕምሮ ሀኪሞች(ከተገኘ)፣ የሕክምና ባለሙያዎችንና ዐቃቤ ህጎችን ያካተተ ይሆናል፡፡

በዚህ ሁኔታ የግለ-ታሪክ ምርመራው የሚጀምር ሲሆን የግል ፋይል(ሰነድ) ለተጎጂዋ ይከፈትና ጥብቅ በሆነ ሚስጥራዊ አያያዝ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ፋይሉ በኤክስፐርቶች በፅሁፍ የተሰባሰቡ የዳሰሳ ጥናቶችን፣ የቃለ መጠይቁን ውጤቶች፣ ሌሎች የተሰባሰቡ መረጃዎችንና የግለታሪክ ምርመራ ቡድኑ የስብሰባ ውጤቶችን ይይዛል፡፡ ሁሉም የተሰበሰቡ መረጃዎች ደረጃቸውን በጠበቁ ቅጾች ተሞልተው ይያዛሉ፡፡

## ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች ቃለ-መጠይቅ ስለማድረግ፡-

### የስነምግባር መርሆዎች

ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች ቃለ-መጠይቅ በፖሊስ፣ በጤና ሰራተኞች/ባለሙያዎች፣ ከተጎጂዎች ጋር የሚሰሩ ድርጅቶች በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ፣ በፍርድ ቤት፣ ወዘተ… ሊደረግ ይችላል፡፡ በየደረጃው የሚደረጉ ቃለ መጠይቆ ተጎጂዎችን በህሊና ቁስል ሲሰቃዩ የቆዩ በመሆናቸው ለዳግም ጥቃት እንዳይጋለጡ በጥንቃቄ የቃለ-መጠይቅ አደራረግ ስነምግባርን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ከተጎጂዎች ጋር ቃለመጠይቅ ለማድረግ በሚከተሉት መርሆዎች ላይ በመመስረት በጥንቃቄ መደረግ አለበት ፡-

- *የቃለ መጠይቁ የጊዜ እርዝማኔ* ፡-ሪፖርቶችን ለማዳበርና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ስሜታቸውንና ንዴታቸውን መግለጽ በሚያስችል አጭር ጊዜ ውስጥ መከናወን አለበት፡፡
- *ቃለ መጠይቅ የሚደረግበት ቦታ*- ተጎጂዎችን ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ በነሱ ምርጫ ዘመዶቻቸው እንዲገኙ ካልፈለጉ በስተቀር ብቻቸውን ሰዎች በማይገኙበት የግል ክፍል ውስጥ ፀጥታ በሰፈነበት ሁኔታ መካሄድ ይኖርበታል፡፡
- *ግልጽና አጭር ጥያቄዎች*፡- ግልጽ፣ አጭርና ቀጥተኛ የተመጠኑ ጥያቄዎችን መጠየቅ የቃለ-መጠይቁን ጊዜ ያሳጥራል፣ ተገቢውን የሚፈለጉ መረጃዎችንም ለማግኘት ይረዳል፡፡
- *ገደብ የማያደርጉ ጥያቄዎች*- ምንም አይነት ገደብ የማያደርጉ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- *ተጎጂዋ የተናገረችውን መድገም*፡- ቃለ-መጠይቁን የሚያደርገው ሰው ተጎጂዋ የምትሰጠውን መረጃ ማዳመጡን እና መረዳቱን ለማሳወቅ የተናገረችውን ነገር አልፎ አልፎ በራሱ አባባል መድገም
- *ማበረታታት*፡- ቃለ-መጠይቁን የሚያደርገው ሰው ተጠያቂዋን በቃልም በአካል እንቅስቃሴም ስሜቷን በሚገባ እንድትገልጥ ማበረታታት ፡-
  - ✓ በቅድሚያ እራስን ማስተዋወቅ፡፡ ተጎጂዋ ከቤተሰቦቿ አባል ጋር መሆን እንደምትፈልግና እንደማትፈልግ ማረጋገጥ፡፡
  - ✓ ተጎጂዋ ነጻነት እንዲሰማትና የምታውቀውን ብቻ እንድትተርክ በሁኔታዎች ወይንም በአጋጣሚዎች ላይ ግምታዊ አስተያየቷን መግለጥ እንደማይገባት መንገር፡፡ ማንኛውም የተነጋገሩባቸው ጉዳዮች በሙሉ አስተማማኝ በሆነ ሚስጥር እንደሚያዙ መንገር፡፡
  - ✓ በቆይታችሁ ጊዜ ቤተሰባዊ የሆነ ስሜት እንዲፈጠርና ዘና እንድትል ሌሎች ጉዳዮችን ለምሳሌ ምን መስራት እንደምትወድ ወዘተ. መጠየቅ፡፡
  - ✓ በቅርብ ጊዜ ምን ትሰራ እንደነበረ ወይንም ምን አይነት ገጠመኝ እንደነበራት በመጠየቅ የማስታወስ ችሎታዋን ማጎልበት
  - ✓ በማስከተል እዚህ በመጣችበት ጉዳይ ላይ ቀለ-መጠይቅ ልታደርግላት እንደምትፈልግ መንገር
  - ✓ የገጠማትን በምትተርክበት ወቅት ንግግሯን አለማቋረጥ
  - ✓ ተጠያቂዋ ምላሽ የማትሰጥ ከሆነ ወይንም የሚጠበቀውን አይነት መረጃ እንደተጠበቀው ከሰጠች ስለጉዳዩ በዝርዝር ለማወቅ የሚረዱ መሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡

- *ዝምታ*:- ተጎጂዋ ከረጅም ጊዜ በፊት የገጠማትን ማስታወስ እንድትችል በዝምታ ጊዜ መስጠት
- *መከለስ*:- ከቃለ-መጠይቁ መጨረሻ የተነገረውንና ውይይት የተደረገባቸውን ጉዳዮች መከለስ፡፡ ይሄ የሚረዳው ለተጎጂዋ የተናገረችውን ሁሉ በሚገባ እንደተደመጠች ዋስትና የሚሰጣት ሲሆን ጠያቂውም የተነገረውን በሙሉ በሚገባ የተረዳ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
- *አስተማማኝነት* :- ጠያቂው ከተጎጂዋ የተገኙት መረጃዎች በሙሉ የሌሎች ባለሙያዎች ተሳትፎ አስፈላጊ ሆኖ እስካልተገኘ-ድረስ ሚስጥራዊነቱ በአስተማማኝ ሁኔታ ተጠብቆ እንደሚቀመጥ ማረጋገጥ፡፡
- *አለመታዘብ/አለመገመት*:- ለተጎጂዋ ቃለመጠይቅ በሚደረግበት ወቅት ጠያቂው የመተቸት ወይንም የመታዘብ- እንደመበሳጨት አይነት ስሜት ማሳየት የለበትም፡፡

## ስሜታዊ ድጋፍ መስጠት

በወሲባዊ ጥቃት አማካይነት ከሚከሰቱትና እጅግ አሰቃቂና ቶሎ ከማይቀረፉት ችግሮች አንዱ በተበዳይዋ ላይ የሚከሰተው የስሜት መረበሽና የስነ-ልቦና ጉዳት ነው፡፡ የተጊጂዋን የስሜት ሁኔታ መረዳት መቻል ብቻ በራሱ "የመጀመሪያ እርዳታ" ስለሆነ የደረሰውን የስሜት ጉዳት የመፈወስ ሀይል አለው፡፡

*ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች በአብዛኛው የሚያንጸባርቋቸው ስሜቶች* -

- ከፍተኛ (ከልክ ያለፈ) ጭንቀት
- ማህበራዊ ግንኙነትን መሸሸ
- በከፍተኛ ሁኔታ መቆጣት (ቁጡነት)
- ድንገተኛ የስሜት መለዋወጥ
- ድብርት (የስሜት መደንዘዝ)
- የማንነት ክስረት
- የጥፋተኝነትና የሀፍረት ስሜት
- የበታችነት ስሜት
- የፍርሀት ስሜት
- የሀዘን ስሜት ናቸው፡፡ ሁሉም ወሲባዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ተጎጂዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት ከላይ የተዘረዘሩት የስሜት መረበሾች ወሲባዊ ጥቃት

በደረሰባቸው ተጎጂዎች ላይ የሚንጸባረቁ መሆናቸውን በመረዳት ችግራቸውን በነሱ ቦታ ሆኖ ርህራሄ በተሞላበት መንፈስ ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## ፈጣን የሆነ ተግባራዊ እርምጃና የቅብብሎሽ አገልግሎት

በአጠቃላይ የመጀመሪያውን የወሲባዊ ጥቃት አጋጣሚ ከተጎጂዋ ገለጣ (ሪፖርት) የተቀበለ ሰው ከላይ በተገለጠው የቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴ በእያንዳንዱ ጣቢያ ምቹ ሁኔታዎችን ያካተተና ወደፊት የሚቀጥል ወይንም ባለበት የሚጠቃለል አገልግሎት መሰረት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች ከተሰባሰቡና ጥልቅ መረጃዎች በውል ተለይተው በቅደም ተከተል ከተለዩ በኋላ ቀዳሚው የድጋፍ አገልግሎት በአደጋው ላይ ትኩረት በማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የአደጋ መከላከሉ አሰራር ከመነሻው ላይ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አላማው መሆን ያለበት በተጎጂዋ ላይ ጫና እንዳይፈጠር በአካልም፣ በስሜትና በማህበራዊ ደህንነት እንዲሰማቸው በማድረግ ቀስ በቀስ ደረጃ በደረጃ መረጋጋት እንዲፈጥሩና ሁኔታውን መቆጣጠር እንዲችሉ መርዳት፡፡ የጤና ድጋፍ ወሲባዊ ጥቃትን ያካተተ አደጋ ሲያጋጥም በመጀመሪያ ደረጃ ሊሰጥ የሚገባው ሲሆን የአካል ጉዳት የደረሰባቸውም

ከሆነ በአንድ ላይ ይረዳሉ፡፡ የደረሰው ጥቃት አስገድዶ መድፈር ከሆነ በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የክሊኒክ አሰራር መመሪያ መሰረት ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን የአካል ጉዳት ሕክምናን ጨምሮ የድንገተኛ እርግዝና መከላከያ እንክብል፣ ለኤች.አይ.ቪ. ከተጋለጡ በኋላ የሚሰጥ የመከላከያ መድሀኒት ወዘተ. ይሰጣል፡፡ እኩል ጠቀሜታ ያለው ለተጎጂዎች የሚሰጠው ልዩ ድጋፍ ከፍትህ ስርአቱ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ስትጀምርና የህግ አሰራር ሂደት በአብዛኛው በመጀመሪያው ወሳኝ ሰአት ላይ መሰጠት ይጀምራል፡፡ አገልግሎት ሰጪዎች ለተጎጂዋ ምን አይነት አገልግሎት እንደምታገኝና ምን እንደማታገኝ ወይንም በየትኞቹ አገልግሎቶች የተወሰነ

አገልግሎት እንደምታገኝ ትነገራለች፡፡ ይሄም የተሳሳተ ተስፋ ግምት እንዳይኖራት ይረዳታል፡፡ ሁሉም በቅብብሎሽ የአሰራር ስርአት ሂደት ውስጥ ያሉ አገልግሎት ሰጪዎች ተጎጂዋን በሚልኩበት ጊዜ ምን አይነት አገልግሎት በየትኛው አካል እንደሚሠጥ በቂ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በዚህ ደረጃ አስገድዶ መደፈር የደረሰባት ተጎጂ ለአደጋ በተጋለጠችበት ወይንም ስጋት በሚፈጥር ሁኔታ ውስጥ ካለች የመጀመሪያ

ደረጃ የጥበቃ አገልግሎት ለምሳሌ ለአደጋ ከሚያጋልጥ አካባቢ ማራቅና ምቹ ወደ ሆነ ቦታ ለምሳሌ መጠለያ ክፍል ውስጥ እንድትቀመጥ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይሄንን አገልግሎት ለመስጥት በዕዝል-2 ላይ የሰፈረውን የቅብብሎሽ ቅፅ መጠቀም፡፡

## ደህንነቱ የተጠበቀ ማረፊያ ቤት

ደህንነታቸው የተጠበቀ ማረፊያ ቤቶች የሚቋቋሙበት አላማ ወሲባዊ ጉዳት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች ሰላማዊና ደህንነቱ የተጠበቀ ጊዜያዊ የማረፊያ አገልግሎት ለመስጠት ነው፡፡ አገልግሎቱ የሚሰጠው ጥቃቱን የፈጸመው ተጠርጣሪ የቤተሰብ አባል፣ የቅርብ ስጋ ዘመድ፣ አሰሪያቸው ወይንም ጎረቤት ሲሆንና ጥቃቱ የተፈጸመባት ተጎጂ ምንም አይነት ድጋፍ የሚያደርግላት ሰው የሌላት ሆና ስትገኝ ነው፡፡ እንዲቆዩ የሚደረገውም የህግ ሂደቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስና ወደ ቤተሰብ፣ ቤተዘመድ፣ ተቋም (አገልግሎት መስጫ መአከል) ፣ ወዘተ. እስከሚቀላቀሉ ድረስ ነው፡፡ የማረፊያ ቤቱ ከመጠለያ አገልግሎት በተጨማሪ የምግብ ፣ የአልባሳት፣ የምክክር አገልግሎት፣ የህክምና እና የክህሎት ስልጠና ወዘተ. አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡

## 4.2. ተቋማዊ ልዩ ምላሽ

### የጤና/የህክምና ምላሽ

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከጤና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎቶች በሁሉም ስፍራ እንዲገኙ፣ ተደራሽነታቸው እንዲጨምርና የህብረተሰቡን አቅም ያገናዘበ አገልግሎት ለመስጠት ደረጃውን ጠብቆ የተዘጋጀ አሰራር አለው፡፡ ጎን ለጎን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና የጤና ልማት ሰራዊት መሰረታዊ የጤና ፓኬጅ አገልግሎቶችን በመያዝ እያንዳንዱን ቤተሰብ መድረስ በመቻላቸው የጤናውን ዘርፍ ግብ በከፍተኛ ደረጃ ምቹ አድርገውታል፡፡ ይሄ አደረጃጀትና ስርአት ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

የወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የተዘጋጀው ብሄራዊ የአመራር መመሪያ ይሄንን ሰነድ የሚያጎለብት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች በሪፈራል፣ በአጠቃላይና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ የግል ሆስፒታሎችና የፅንስና ማህፀን ልዩ ማእከሎች፣ ክሊኒኮች ወይንም መካከለኛ ክሊኒኮች ሀኪሞች በሚገኙባቸው ተቋማት ሁሉ አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች የሚከተሉትን የጤና አገልግሎት በሚሰጡ ጤና ባለሙያዎች ሊገለገሉ ይችላሉ፡-

- በፅንስና ማሕፀን ስፔሻሊስቶችና በሐኪሞች
- ልዩ ስልጠና በተሰጣቸው መካከለኛ ደረጃ የህክምና ባለሙያዎች (ጤና መኮንኖች፣አዋላጅ ነርሶችና ነርሶች)
- ወንድ ተጎጂዎች በሕጻናትና በቀዶ ህክምና ስፔሻሊስቶች ምርመራ ሊደረግላቸውና ህክምና ሊያገኙ ይገባል
- ጥቃት/አስገድዶ መደፈር የደረሰባቸው ህፃናት በፅንስና ማሕፀን ስፔሻሊስቶችና በህጻናት ሕክምና ስፔሻሊስቶች ምርመራ ሊደረግላቸው ይገባል
- የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸው ተጊጂዎች በአእምሮ ሐኪም እና በአእምሮ ህክምና ነርስ ሊረዱ ይገባል
- በህግ አስከባሪ አካላት እድሜን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ራዲዮሎጂስቶች እንዲሳተፉ ይደረጋል
- የሥነልቦና/የአእምሮ ህክምና ባለሙያዎች በምክክርና በድጋፍ አገልግሎት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች በሙሉ በወሲባዊ ጥቃት የሚሰቃዩ ተጎጂዎች ለሌላ የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለማግኘት፣ ስለራሳቸው ችግር ሪፖርት ለማድረግ፣ ታጅበው ሲመጡ፣ በሌላ ሰው ሪፖርት ሲደረግ ወይም በቅብብሎሽ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት ከሌላ አካል ለምሳሌ ከፖሊስ፣ ከሴቶች ቡድን ወዘተ. ወደ ጤና ተቋም ሲመጡ እንዴት ተጎጂዎቹን መለየት እንደሚችሉ፣ ትክክለኛ ሪፖርት እንደሚያዘጋጁና ለተገልጋዮቻቸው ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችሉ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ሁሉም ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች አገልግሎት ለማግኘት ወደ ጤና ተቋም ሲመጡ በድንገተኛ የህክምና አሰጣጥ ስርአት መሰረት ያለምንም ክፍያ የተሟላ አገልግሎት ማግኘት አለባቸው፡፡ ጤና ተቋማት የተጎጂዎችን ግላዊ ማንነትና ሚስጥራቸው በአስተማማኝ ሁኔታ ተጠብቆ አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበት የተለየ ክፍል ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## የተጎጂዎችን ሚስጢር በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅ ለሚከተሉት መርሆዎች ትኩረት መስጠት

- ✓ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ማንም ሰው ከቤተሰብና ከጠባቂዎች(ሞግዚቶች) በስተቀር ወደ ምርመራ ክፍሉ መግባት አይኖርባቸውም፡፡
- ✓ በተቋም ውስጥም ሆነ ከተቋም ውጪ የመረጃ ልውውጥ በሚደረግበት ወቅት መለያ ስምን ከመጠቀም ሚስጥራዊ መለያ (ኮድ) መጠቀም፡፡
- ✓ ፖሊሱ፣ ጉዳቱን ያደረሰው ሰውና ቤተሰቦቹ ወደ ምርመራ ክፍሉ መግባት አይኖርባቸውም፡፡ ነገር ግን በሌላ ክፍል እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡
- ✓ አስተርጓሚዎችና የማህበራዊ ሳይንስ ሰራተኞች ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ ከተደረገ በኋላ የስነ-ምግባር ደንብ እንዲፈርሙ ማድረግ፡፡
- ✓ ከወሲባዊ ጥቃት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ግዴታ አስፈላጊ ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ከሌላ የስራ ባልደረባ ጋር አለማውራት
- ✓ የተጎጂዋ ግለ-ታሪክ በሚቀርብበት ወቅት፣ ስለተጎጂዋ በመኝታዋ ዙሪያ ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት፣ በአመራሩ ስብሰባ ላይና ለጤና ትምህርት ሰልጣኞች ትምህርት ለመስጠት አጠቃላይ ጉብኝት በሚደረግበት ወቅት የተጎጂዋን ማንነት የማያመለክት ሚስጥራዊ መለያ መጠቀም፡፡
- ✓ በተቻለ አቅም ለተጎጂዋ አገልግሎት ለመስጠት የተመደበችዋን(ውን) ባለሙያ ማንነት ጥቃቱን ካደረሰው ሰው ጋር ትውውቅ መደረግ አይኖርበትም፡፡
- ✓ የጤና አገልግሎት ባለሙያዋ(ው)ና ተጎጂዋ አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀር በፎቶግራፍ፣ በድምፅም ሆነ በምስል(ቪዲዮ) ተቀርፀው እንዲታወቁ መደረግ አይኖርበትም፡፡
- ✓ ሁሉም የተሞሉ ቅጾች፣ የግለ-ታሪክ ማስታወሻዎች፣ መዛግብቶችና በተጨማሪም ማንኛውም አይነት ፎቶዎች፣ የድምፅ መቅረጫዎችና የቪዲዮ ክሮች በሙሉ ጥቅም ላይ ውለው እንዳበቃ አስተማማኝ በሆነ የሚቆለፍ ካቢኔት ውስጥ ተቆልፈው መቀመጥ አለባቸው፡፡
- ✓ በቃለ-መጠይቅ ወቅት ድምፅና ምስል የተቀረፀባቸው ካሴቶች ቃለ-መጠይቁ ወደ ፅሁፍ ተቀይሮ እንዳበቃና የፍርድ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከላይ በተጠቀሰውአግባብ ጥበቃ እንዲደረግለት በማድረግ ከፍርድ ሂደቱ በኋላ እንደአስፈላጊነቱ ማስወገድ፡፡ (ዳግመኛ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ማድረግ)፡፡
- ✓ የአመራር መመሪያውን የሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ በመጠቀም ገጠመኞች በሙሉ ተመዝግበው እንዲቀመጡ ማድረግ

## የጤና ባለሙያዎች ወሲባዊ ጥቃት ሲደረሰባቸው ተጎጂዎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናውናሉ

1. ትክክለኛውን ታሪክ መቀበል
2. አካላዊ ምርመራ ማድረግ
3. ለላቦራቶሪ ምርመራ ናሙና መውሰድ
4. ለህግ የሚያገለግሉ መረጃዎችን ማሰባሰብ

5. ለአባለዘር በሽታዎች፣ ለኤች.አይ.ቪ.፣ ለሄፓታይተስ-ቢ፣ ኢንፌክሽኖችና ለሌሎችም እንደ ቴታነስ ላሉት ተገቢውን የመከላከልና የማከም አገልግሎት መስጠት
6. ለተጎጂዎች የምክክር አገልግሎት መስጠት
7. በሂደቱ ላይ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ
8. ጥቃቱ የደረሰባቸውን አጋጣሚዎች መዝግቦ መያዝ
9. የሕክምና ምስክር ወረቀት ማዘጋጀት
10. ለሕግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት ማድረግ
11. ወደ ሌላ አካላት (ለማህበራዊ ስነልቦና አገልግሎት፣ ለሕግ ድጋፍ፣ ለጥበቃ ቤት፣ ወዘተ) ማስተላለፍ፡፡
12. በአመራሩ መመሪያ መሰረት ክትትልና ግምገማ ማካሄድ
13. ለመርሆዎቹ ታማኝ በመሆን ፡-
    - ደህንነት
    - አስተማማኝ የሚስጥር ጥበቃ
    - አክብሮትን ያለምንም መድሎ ለሁሉም መስጠት፡፡

## በየደረጃው በሚገኙ ጤና ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች

| ተ.ቁ | የጤና ተቋሙ ደረጃ | የሚሰጠው የአገልግሎት አይነት |
|---|---|---|
| 1 | ጤና ኬላ | ጌ◉9 መለስተኛ ቁስሎችን ማጠብና መጠቅለል(ድሬስ ማድረግ)<br>ጌ◉9 አቅም ለሚፈቅድላቸው ተጎጂዎች የድንገተኛ እርግዝና መከላከያ እንክብል እንዲወስዱ ማድረግ<br>ጌ◉9 ለህዝባዊ ፖሊስ፣ ለሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሪፖርት ማድረግ<br>ጌ◉9 ያካባቢውን ሽማግሌዎች ወይም ባህላዊ ሕጎችን በመጠቀም ግጭቶችን ለማስወገድ ጥረት ማድረግ<br>ጌ◉9 ተጎጂዎችን በአቅራቢያ ወደሚገኝ ጤና ጣቢያ ማስተላለፍ<br>ጌ◉9 በወሲባዊ ጥቃት ላይ ስልጠና መውሰድ |
| 2 | ጤና ጣቢያ | ጌ◉9 ሁሉንም የጤና ኬላ ሀላፊነቶች ማከናወን<br>ጌ◉9 በወሲባዊ ጥቃት ላይ የሰለጠነ ባለሙያ ሊኖር ይገባል<br>ጌ◉9 ጠቀሜታ ያላቸውን ታሪኮች መቀበል፣ አካላዊ ምርመራ ማድረግ፣ የላቦራቶሪ ምርመራ ማድረግ<br>ጌ◉9 ከሴቷ ብልት ያልደረቀ የዘር ፈሳሽ መውሰድ<br>ጌ◉9 ለአባለዘር በሽታዎች የመከላከያና የህክምና አገልግሎት፤ ለኤችአይቪ የድህረ-ኢንፌክሽን መከላከያ መድሀኒት መስጠት<br>ጌ◉9 በአስገድዶ መደፈር ምክንያት የተፈጠረን እርግዝና በመጀመሪያው ሶስት ወር ላይ ማስወገድ<br>ጌ◉9 በአካል ላይና በብልት አካባቢ የተፈጠረን ቁስል ማከም፣ የቲ.ኤቲ.ና የሄፓታይተስ-ቢ ክትባት መስጠት<br>ጌ◉9 የምርመራ ግኝቶችን በተጊጂዋ መዝገብ ላይ በመመዝገብ ሚስጥራዊነቱ ተጠብቆ እንዲቀመጥ ማድረግ<br>ጌ◉9 የህክምና ምስክር ወረቀትና ተጨማሪ የህክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ወደ ሆስፒታል ማስተላለፍ<br>ጌ◉9 ተጎጂዎችን ለማህበረሰባዊ ስነልቦናና ለሕግ የድጋፍ አገልግሎት ማስተላለፍ |

| | | |
|---|---|---|
| | | - ለተጎጂዎች ድጋፍ የሚሰጡ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለይቶ ማወቅ<br>- የጥቃቱን አጋጣሚዎች በአቅራቢያ ለሚገኝ ፖሊስ ሪፖርት ማድረግ |
| 3 | የመጀመሪያ ደረጃ አጠቃላይ ሆስፒታል | - ሁሉንም የጤና ጣቢያ አገልግሎቶች ማከናወን<br>- በሆስፒታሉ ውስጥ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች እንክብካቤ የሚደረግበት ልዩ ክፍል ማቋቋም<br>- የህግ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ<br>- በሆስፒታል ደረጃ የሚሰሩ በአካል ላይ እና በብልት አካባቢ የደረሰን ጉዳት ማከም፡፡ የቲ.ኤቲ.ና የሄፓታይተስ-ቢ ክትባት መስጠት<br>- ለአባለዘር በሽታዎችና ለኤች.አይ.ቪ. የመከላከያና የህክምና አገልግሎት መስጠት<br>- በአስገድዶ መደፈር ምክንያት የደረሰን እርግዝና በመጀመሪያውና በሁለተኛው ሶስት ወራት ውስጥ ማስወገድ፡፡ ተጎጂዋ እርግዝናው እንዲቀጥል ከፈለገች ተገቢውን አገልግሎት መስጠት<br>- የህክምና የምስክር ወረቀት ሲዘጋጅ<br>  • ግልፅ የሆኑ ገላጭ ቃላትን መጠቀም<br>  • ተጨባጭ የሆኑ ሁኔታዎችን መጠበቅ<br>  • በሙያ ደረጃ ላይ መወሰን<br>  • ስሜታዊ አስተያየቶችንና ተጨባጭ እውነታዎችን መለየት<br>  • የተሰበሰቡ ናሙናዎችን መዘርዘር<br>  • በድጋሚ በፍርድ ቤት በመሀላ ቃል ለመስጠት የተዘጋጀሽበትን/ህበትን ብቻ ማለት ወይም መጻፍ<br>  • አገልግሎቱን በሰጠው ጤና ባለሙያ የሚዘጋጀው የሕክምና የምስክር ወረቀት በአካባቢው የመግባቢያ ቋንቋ መሆን ይኖርበታል<br>  • የሕክምና አገልግሎቱን የሰጠው ባለሙያ የአካባቢውን ቋንቋ የማያውቅ ከሆነ በሌላ ቋንቋውን በሚያውቅ ባለሙያ በማስተርጎም የምስክር ወረቀቱ መዘጋጀት አለበት<br>  • የሕክምና የምስክር ወረቀቱ ማጠቃለያ ሊኖረው ይገባል (ለምሳሌ በአካልም ላይ ሆነ በብልት አካባቢ ቁስል አለመኖር ጥቃቱ አልተፈጸመም ማለት እንዳልሆነ፤ ጥቃት በደረሰባቸው ልጆች በላቦራቶሪ ምርመራ ኒሴሪያ ጎኖሬ መገኘት በእርግጠኝነት ጥቃት የተፈጸመ መሆኑን የሚያመለክት ስለመሆኑ፤<br>  • ለፖሊስና ለፍርድ ቤት የሚቀርብ የህክምና ምስክር ወረቀት በ48 ሰአታት ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የሚዘገይም ከሆነ ስለመዘግየቱ በቂ ምክንያት ማቅረብ ያስፈልጋል<br>  • የሪፖርት ማድረጊያ ቅፁን በአመራር አካሉ መመሪያ ላይ በሰፈረው መሰረት መጠቀም፤ ወይንም ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ መጠቀም<br>  • ሪፖርቱን ለፖሊስ ወይንም ለተገልጋዩ በሰም በታሸገ ኤንቬሎፕ አሽጎ መስጠት<br>  • በሰም በታሸገው ኤንቬሎፕ ላይ “በሚመለከተው ሕጋዊ አካል ከተከፈተ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል!!” የሚል ፅሁፍ ማስፈር<br>  • ከተገልጋዩ መዝገብ ጋር ተያይዞ የሚቀመጥ የሪፖርቱን አንድ ኮፒ(ቅጂ) ማስቀረት<br>  • የተጎጂውን መዝገብ በሚቆለፍ ካቤኔት ውስጥ ቆልፎ በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግ<br>  • የፋይል ካቢኔቱ ቁልፍ በሚታመን ሰው እጅ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | ጌ◉9 የመጀመሪያ ደረጃ አጠቃላይ ሆስፒታል አገልግሎቶችን መተግበር<br>ጌ◉9 የፅንስና የማሕፀን ምርመራ አጉልቶ በሚያሳይና ፎቶ በሚያነሳ መሳሪያ (colposcopic evaluation) ብልት ላይ ለደረሰ መለስተኛ ቁስል ማካሄድ<br>ጌ◉9 የፅንስና ማሕፀን ሕክምና ባለሙያዎች ለህግ(ድንግል) መደፈር፣ በብልት ላይ ለደረሰ ከፍተኛ ጉዳትና ኢንፌክሽን ምርመራ ማካሄድ<br>ጌ◉9 ለተወሰኑ ተጎጂዎችና ጥቃት ፈጻሚዎች የጭንቅላታቸውን የጤንነት ሁኔታ ለማወቅ በአእምሮ ሃኪም ምርመራ ይደረጋል<br>ጌ◉9 የስነ-አእምሮ ጤና ክትትል የአእምሮ ጤና መታወክ ለደረሰባቸው ይደረጋል<br>ጌ◉9 በቀዶ ሕክምናው ሐኪም በፊንጢጣና በውስጠኛው አካል ላይ የደረሰን አደጋ (ano-ectal injuries) የ ano-proctoscopic ምርመራ (የራሱ ብርሀን ባለውና ቱቦ ቅርፅ ባለው የህክምና መሳሪያ በፊንጢጣ በኩል በማስገባት የውስጠኛውን አካል መመርመር) ለሚያስፈልጋቸው ይደረጋል<br>ጌ◉9 የራዲዮሎጂ ምርመራ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ይደረጋል<br>ጌ◉9 ለሕግ አካል የሚቀርቡ መረጃዎችን ለምሳሌ የዘረመል (DNA) ምርመራ ይደረጋል<br>ጌ◉9 ሙሉ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ መስጠት የሚያስችል መአከል መመስረት፤ ልዩ ክሊኒኮችን ማቋቋም፤ ምርጥ ተሞክሮዎችን እየቀመሩ ማስፋፋት፡፡ |

## በህክምና ባለሙያዎች ለህግ አስፈጻሚ አካላት የሚሰጥ የህክምና ምስክር ወረቀት

- ✓ የህክምና ምስክር ወረቀቱ በሆስፒታል ደረጃ መሰጠት አለበት
- ✓ የህክምና ምስክር ወረቀቱ በ48 ሰዓታት ውስጥ ዝግጁ መሆን አለበት
- ✓ ከፍተኛ የሆነ የጤና ክብካቤ ሰጪ ባለሙያ የህክምና ምስክር ወረቀቱን የመስጠት ኃላፊነት አለበት
- ✓ የጤና አገልግሎቱ የህክምና ምስክር ወረቀቱን ከመጻፉ በፊት የፖሊስ መጠየቂያ ማግኘት አለበት
- ✓ የህክምና ምስክር ወረቀት በሚጻፍበት ወቅት ሁሉም የህክምና ባለሙያዎች በዚህ ደረጃውን የጠበቀ የአተገባበር ስርዓት ሰነድ ላይ አባሪ በተደረገው የሪፖርት ማድረጊያ ቅጽን መጠቀም አለባቸው
- ✓ የህክምና ምስክር ወረቀቱ በአካባቢው በስራ ላይ በዋለው ቋንቋ መጻፍ አለበት
- ✓ የተጎጂዋ ወይም ተጎጂው ስም፣ እድሜ፣ ጾታ እና አድራሻ በምስክር ወረቀቱ ላይ በግልጽ መቀመጥ አለበት
- ✓ የተጎጂዋ ታሪክ በአጭሩ መገለጽ አለበት
- ✓ አግባብነት ያለው የአካላዊ ምርመራ በሰነድ ላይ መስፈር አለበት
- ✓ የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት በምስክር ወረቀቱ ላይ መጠቀስ አለበት
- ✓ በምስክር ወረቀቱ መጨረሻ ላይ ማጠቃለያ መሰጠት ያስፈልጋል
- ✓ በምስክር ወረቀቱ ሳይንሳዊ አገላለፆች በመጠቀም የደረሰውን ጉዳት ማመልከት እንጂ በህግ አካላት/በፍ/ቤት አካላት ብቻ ውሳኔ ሊሰጡባቸው በሚችሉና ድምዳሜ ላይ በሚያደርሱ እንደ ተገዶ መደፈር የመሳሰሉ የህግ ቃላት መገለፅ የለበትም
- ✓ የምስክር ወረቀቱን የመስጠት ኃላፊነት ያለው የህክምና ባለሙያ በምስክር ወረቀቱ ግርጌ ላይ በግልፅ ስሙን መጻፍ እንዳለበት እና ፊርማውንም ማኖር አለበት

- ✓ በምስክር ወረቀቱ ላይ ማህተም ማረፍ አለበት፣ ማህተም ያረፈበት የምስክር ወረቀት በፖስታ ታሽጎ በታሸገው ፖስታ ላይም መከፈት የለበትም የሚል ሀረግ ሊጠቀስ ይገባዋል
- ✓ የምስክር ወረቀቱ ለፖሊስ መሰጠት አለበት
- ✓ ፖሊሱም የምስክር ወረቀቱን የተረከበ መሆኑን ለማረጋገጥ ፊርማውን ማኖር አለበት
- ✓ በህክምና ምስክር ወረቀቱ ላይ አሻሚ የሆኑ ቃላት መጠቀም እንደማይገባ እና የምስክር ወረቀቱም የፍርድ ቤት መስማት ሂደቱን ሊያግዝ በሚችል ሁኔታ መዘጋጀት ያስፈልጋል

✓ የህግ አስከባሪ አካላት ሙሉ በሙሉ በክብረ ንፅህና ምርመራ ውጤት ላይ መተማመን እንደሌለባቸው ይልቁንም ሰነዱ አጋዥ ማስረጃ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የህክምና ባለሙያዎች ማስረጃ በሚፅፉበት ወቅት የክብረ ንጽህና ምርምራ ውጤት ከመግለፅም ባሻገር ተጨማሪ የማጠቃለያ ዓረፍተ ነገር ሊያስቀምጡ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ክብረ ንፅህናቸው ላይገሰስ (ላይጎዳ) ይችላል፡ ፡ በዚህ ምክንያት ክብረ ንፅህና አልተገሰሰም ተብሎ ወንጀለኛው ነፃ መለቀቅ እንደሌለበት በማጠቃለያ ሃሳባቸው ላይ ሊያሳዩ ይገባል፡፡ ይህንንም ሁኔታ በሁሉም ማስረጃ በሚፅፉ የጤና ባለሙያዎች ሊተገበር ይገባል፡፡

## በፖሊስ የሚሰጥ ምላሽ

የጤና ባለሙያው ለህግ አስፈጻሚ አካላት ሪፖርት የሚደረጉ መረጃዎችን በሚያዘጋጅበት ወቅት ታሳቢ መደረግ የሚገባቸው ጉዳዮች፡-

- ሪፖርት በሚደረገው ጉዳይ ላይ ድጋፍ ሊሰጡና ቀጣይ ክትትል ሊያደርጉ የሚችሉ የተፈላጊ አካላትን አድራሻ፣ ወኪልና መረጃ ማወቅ
- በሕጉና በፖሊሲው መሰረት ጥቃቱ የደረሰበትን ሁኔታ ሪፖርት የማድረጉን ጠቀሜታ ለተጎጂዎች ማስረዳት
- የአስገድዶ መደፈር የደረሰባቸውን ተጎጂዎች አጋጣሚዎችና ማንኛውንም አይነት የቤት ውስጥ የጥቃት ሁኔታዎች በአስቸኳይ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ
- ስለደረሰው አደጋና ገጠመኝ ሪፖርት በሚያደርገው አካል የፖሊስ ጣቢያዎች የስልክ ቁጥር ዝርዝር እንዲቀመጥ ማድረግ
- አደጋው ስለደረሰበት ሁኔታ ተጎጂዋ በገለጠችው መሰረት በፅሁፍ ሰነድ ላይ ማስፈር
- ጥቃቱን ተከትለው ሊከሰቱ ስለሚችሉ ተከታታይ ሁኔታዎች ለተጎጂዎቹ ማስረዳት
- የህፃናቱን ጉዳት ሪፖርት ማድረግ በሚያስከትለው ጠቀሜታና አደጋ መካከል ሚዛናዊ በመሆን ህፃናቱ በሙሉ በወቅቱ ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ
- የህፃናን ዋንኛ ፍላጎት ለማረጋገጥ በመርሆው መሰረት መስራት ይገባል፡፡ ተጎጂዋ ስለደረሰባት ጉዳት ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ካልፈለገችና ጤና ባለሙያው ህፃኗ ለተደጋጋሚ ጥቃት የተጋለጠች ስለመሆኗ እርግጠኛ ከሆነ አንድ ሰው ህፃኗ አደጋ ውስጥ ስለመሆኗ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡በማህል ህፃናን በጥበቃ ስር ለማቆየት ደህንነቱ የተጠበቀ ቤት ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ሪፖርቱ የጤና ባለሙያውን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ማንነቷን/ቱን መግለጥ አይኖርበትም፡፡
- ወሲባዊ ጥቃት የተፈጸመባቸውን አጋጣሚዎች ሪፖርት ለማድረግ በእዝል-2 ላይ በተገለጠው መሰረት የቅብብሎሽ ቅፁን መጠቀም፡፡

## የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ በማይሰጥባቸው አካባቢዎች የፖሊስ የምርመራ አፈጻጸም

- ✓ ተጎጂዋ ወሲባዊ ጥቃት እንዴት እንደደረሰባት ለሌላ ሰው ነግራ በፖሊስ ጣቢያ ለፖሊስ መኮንኑ ካልነገረች ያ የተነገረው ሰው ተጎጂዋ በአቅራቢያዋ ወደሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ሄዳ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደምትችል ትክክለኛውን አቅጣጫ ሊያመላክታት ይገባል፡፡ በተጨማሪ የተነገረው ሰው ስለሁኔታው ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ይችላል፡፡
- ✓ ተጎጂዋ ፖሊስ ጣቢያ እንደደረሰች በመቆያ ክፍል እንድትቀመጥ ይደረጋል፡፡ በማስከተል ጉዳዩን ለመከታተል የተመደበው የፖሊስ መኮንን ( በተቻለ አቅም ለሴት ተጎጂ ሴት የፖሊስ መኮንን እንዲመደብ፤ ለወንድ ተጎጂዎች ምርጫቸውን እዲያሳውቁ በማድረግ) ስርአቱን ያስፈጽማል
- ✓ ተጎጂዋ ስሜቷን ማቀዝቀዝ ከፈለገችና ለመረጋጋት ድጋፍ እንዲደረግላት ከፈለገች ወደ ማሕበራዊ ድጋፍ ወደሚሰጥ ሰራተኛ እንድትተላለፍ ይደረጋል፡፡አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ ተጎጂዋ በአስቸኳይ ምርመራ ልታገኝ ወደምትችልበት በአቅራቢያው ወደሚገኝ ሆስፒታል እንድትተላለፍ ይደረጋል፡፡
- ✓ ከህክምና ምርመራው በኋላ ተጎጂዋ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንድትመለስ ይደረጋል፡፡ ተጎጂዋ ፍቃደኛ ከሆነችና የምትችል ከሆነ የፖሊስ መኮንኑና አቃቤ ህጉ በተገኙበት ቃሏን እንድትሰጥ ይደረጋል፡፡ ካልቻለች የማረጋጋት ድጋፍ እየተደረገላት እንድትቆይ ይደረጋል፡፡

❖ *የፖሊስ መኮንኖቹ የተጎጂዋ ቃል በሚቀበሉበት ወቅት የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ በሚሰጥበት የፖሊስ አሰራር /በክፍል 4.3.2/ ላይ የተገለጠው የቃለ-መጠይቅ አቀራረብ ዘዴና ስርአት መጠቀም ይኖርበታል፡*

## ሁሉም የሴቶችና የህፃናት የፖሊስ የጥበቃ ማዕከላት የሚከተሉትን ግብአቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል

- ✓ ፣- የመቆያ ክፍል፡- የፖሊስ መኮንን እስኪመደብላት ድረስ ተቀምጣ የምትጠብቅበት
- ✓ ፣- የምርመራ ክፍል፡- ፖሊሶችና አቃቤ ሕግ ምርመራቸውን የሚያካሂዱበትና የተጎጂዋን ቃል የሚቀበሉበት
- ✓ ፣- ለማህበራዊ ሳይንስ ሰራተኛው የተለየ ክፍል፡- ማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች ተጎጂዋ ለፖሊስ ቃሏን ከመስጠቷ በፊትና ከሰጠች በኋላ የስነልቦና ዝግጁነት እንድታገኝ ድጋፍ የሚደረግበት
- ✓ መፀዳጃ ቤት
- ✓ የመጓጓዣ አገልግሎት

**መሟላት የሚገባቸው ቁሳቁሶች**፡- ለአዋቂ ተጎጂዎች ከሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በተጨማሪ ከላይ የተዘረዘሩት ክፍሎች ለሕጻናት ምቹ ሆነው የሚከተሉትን እቃዎች ማሟላት አለባቸው

**፩. የመቆያ ክፍል** :- ለሕጻናት እይታ ምቾት በሚሰጥ ቀለም የተቀባ ግድግዳ፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ቴሌቪዥን፣ ወዘተ. የተለያዩ አሻንጉሊቶችና ፎቶዎች፣ የቀለም መቀቢያና የስዕል መሳያ መሳሪያዎች፣ የተለያዩ የልጆች መፅሀፍ፣ የሚጠጣ (ውሀ ወይም ወተት)፣ መቆያ የሚሆን ምግብ (መክሰስ) ፣ የልጆች ፖፖ(የሽንት መቀበያ)፣ የወለል ላይ ፍራሽ፣ ዳያፐሮች፣ የሕጻናት ጡጦ፣ ብልቃጥ፣ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉ ስዕሎችና ፖስተሮች፡፡

2. የምርመራ ክፍል :- ለሕጻናት እይታ ምቾት በሚሰጥ ቀለም የተቀባ ግድግዳ፣ ጠረጴዛና ወንበሮች፣ የተለያዩ አሻንጉሊቶች፣ የስእል መሳያ መሳሪያዎች፣ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉ ስዕሎችና ፖስተሮች፣ የድምፅና የምስል(ቪዲዮ) መቅረጫ መሳሪያዎች፡፡

3. የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው ክፍል :- ለሕጻናት እይታ ምቾት በሚሰጥ ቀለም የተቀባ ግድግዳ፣ ጠረጴዛና 4 ወንበሮች፣ የተለያዩ አሻንጉሊቶች፣ የስእል መሳያ መሳሪያዎች፣ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉ ስዕሎችና ፖስተሮች፣ የወለል ላይ ፍራሾች፡፡

## የሴቶችና የህፃናት የጥበቃ መዐከላት የሚኖራቸው የሰው ሀይል

- ✓ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጊጂዎች 24 ሰአት ክፍት ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በቂ ቁጥር ያላቸው የፖሊስ መኮንኖች
- ✓ የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛ(ኞች) ክፍል :-
- ✓ አስተርጓሚዎች (የምልክት ቋንቋን ጨምሮ)
- ✓ ሾፌር

## የአቃቤ ሕግ ምላሽ

### አፈጻጸም

- ✓ የአቃቤ ሕጉ አስፈላጊ የሆኑ የህክምና ማስረጃዎችን፣ ለፍረድ ቤት የሚቀርቡ ማስረጃዎችን፣ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን በማሰባሰብ የጉዳዩን ሁኔታ በወንጀል ህግ መሰረት ይወሰናል፡፡
- ✓ የአቃቢ ሕጉ የወንጀል ክስ ለመመስረት ከወሰነ በወንጀል ሕጉ በሰፈረው የጊዜ ገደብ መሰረት ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ያቀርባል
- ✓ ተጎጂዋ በተጨማሪ ቃሏን እንድትሰጥ አስፈላጊ ሆኖ በሕግ አስከባሪው/ዋ ከተገኘ ተፈላጊውን መረጃ ለማሰባሰብ ለተጊጂዋ እንክብካቤ የምታደርገውን/ዋን የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛ መጠቀም ያስፈልጋል
- ✓ አቃቤ ህጉ ተጎጂዋ አስፈላጊው የጥበቃና የማህበረሰባዊ ሥነልቦና ድጋፍ እያገኘች መሆኗን ታረጋግጣለች /ያረጋግጣል
- ✓ አቃቤ ህጉ የተጎጂዋን ሰብአዊ መብትና ክብር ያስጠብቃል/ታስጠብቃለች
- ✓ አቃቤ ህጉ ስለ ቀጣይ ሁኔታዎች ለተጎጂዋ/ ለቤተሰቦቿ ታስረዳለች/ል
- ✓ አቃቤ ህጉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የህግ ሂደቱ የዳኞችን ልዩ ክፍል በመጠቀም ፎቶ እንዲነሳና ሚስጥራዊነቱ እንዲጠበቅ ተጎጂዋ ለዳግም የህሊና ቁስል እንዳትጋለጥ ይረዳል፡፡

ይግባኝ/የሕጉን አግባብነት ማረጋገጥ :--ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ በኋላ ተጎጂዋ/ወላጆቿ በፍርድ አፈጻጸሙ ላይ ደስተኛ ካልሆኑና አቃቤ ሕጉ ሌሎች አማራጮች እንዳሉ ከታመነበት የይግባኝ ሂደቱ ሊቀጥል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ይግባኝ ለመጠየቅ ምንም አማራጭ ከሌለ አቃቤ ህጉ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ለተጎጂዋ/ው ወይንም ለጠባቂው/ዋ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ የፍርድ ቤቶች ስርአት ለተጎጂዎች ስነልቦና ጫና የማይፈጥር ቀለል ባለ ከባቢያዊ ሁኔታ ቃላቸውን እንዲሰጡ ጭንቀት/ፍርሀት ሳይሰማቸው ፍትህ የሚስተናገድበት መሆን ይኖርበታል፡፡

## የፍርድ ቤት ምቹ ሁኔታዎች

በተመሳሳይ ሁኔታ የፍርድ ቤቶች ስርአት ለተጎጂዎች ስነልቦና ጫና የማይፈጥር ቀለል ባለ ከባቢያዊ ሁኔታ ቃላቸውን እንዲሰጡ ጭንቀት/ፍርሀት ሳይሰማቸው ፍትህ የሚስተናገድበት መሆን ይኖርበታል፡፡

## የሚያስፈልጉ የሰው ሀይልና ምቹ ሁኔታዎች

### የሰው ሀይል

የሚከተሉት ሰራተኞች በፍርድ ቤት ውስጥ ይገኛሉ

- ✓ ዳኞች
- ✓ አቃቤ ሕጎች
- ✓ ፀሐፊዎች
- ✓ ፖሊሶች
- ✓ አገናኝ ባለሙያ/የማህበራዊ አገልግሎት ባለሙያ
- ✓ አስተርጓሚዎች (የምልክት ቋንቋን ጨምሮ)

## የሚያስፈልጉ ክፍሎች

ፍርድ ከሚሰጥበት ክፍል በተጨማሪ የሚከተሉት ክፍሎች ያስፈልጋሉ፡-

1. ለአዋቂዎችና ለሕጻናት ተጎጂዎች መቆያ ክፍል
2. መካከለኛ ክፍል ፡- ፍርድ ከሚካሄድበት ክፍል ጋር በሲሲ-ቲቪ የተገናኘ ፣ድምፅ የማያስተላልፍ ወይንም ፍርድ ከሚካሄድበት ክፍል ጋር በአንድ አቅጣጫ ብቻ በሚያሳይ መስተዋት የተከለለ ክፍል፡፡

❖ *ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች ምቹ የሆነ ወንበር በእያንዳንዱ የፍርድ ቤት ክፍሎች ውስጥ መኖር ይኖርበታል፡፡*

## ለተጎጂዎች ምቹና ተስማሚ በሆነ ክፍል /መካከለኛ ክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ፡-

1. ለህፃናት እይታ ምቾት በሚሰጥ ቀለም የተቀባ ግድግዳ
2. ወንበር፣ ጠረጴዛና ሶፋ
3. ሲሲ-ቲቪ ከተሟላ እቃው ጋር
4. ማይክሮፎን (ድምፅ ማጉያ)
5. የተለያዩ አሻንጉሊቶች (የተለያዩ መጠን ያላቸውና የሰውነት አካላትን የሚያሳዩ)
6. በግድግዳ ላይ የሚሰቀሉ ስእሎችና ፖስተሮች
7. ምንጣፍ
8. አቅም በፈቀደ ለተጎጂዎች እይታና ስነልቦና ምቾት የሚሰጡ የተለያዩ ነገሮች

### አፈጻጸም

**ሀ)** ክሱ ከተመሰረተ በኋላ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው ለተጎጂዋ የፍርድ ቤት ሂደቱ ምን እንደሚመስል ገለጻ ይደረግላታል ፤ ማንን ልታይ እንደምትችል፣ ወዘተ. የፍርድ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት (በክፍሉ ዝግጅት ወቅት) የፍርድ ቤት ገፅታ ምን እንደሚመስል እንድታይ በማድረግ ፍርሀትና ጭንቀት እንዳይሰማት ስነልቦናዋን ማረጋጋት

**ለ)** የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው ለተጎጂዋ ከፍርድ ሂደቱ በፊትና በኋላ የምክክር አገልግሎት በመስጠት ሊገጥማት የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመጋፈጥና ለመቋቋም እንድትችል ማድረግ፡፡ ሆኖም ግን ተጎጂዋ ከማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛው/ዋ አቅም በላይ የሆነ የምክክር አገልግሎትም ሆነ የህግ ድጋፍ ለማግኘት ከጠየቀች ወደ ሌላ አገልግሎት ሰጪ አካል እንድትተላለፍ ይደረጋል፡፡

**ሐ)**ሌላ የህሊና ቁስል እንዳይፈጠር (ለሁለቱም ለትላልቆችም ለህፃናትም) ቃላቸውን ከመስጠታቸው በፊት ጥቃቱን ፈጽሟል ከተባለው ሰው ሳይተያዩ የሚቆዩበት ለየት ያለ የመቆያ አካባቢ ማስቀመጥ

መ) ተጎጂዋ ህፃን ከሆነች ቃሏን ከተለየ ገለልተኛ ክፍል በአገናኟ ድጋፍ በመታገዝ እንድትሰጥ ይደረጋል፡፡ (ይሄን ሁኔታ አዋቂ ተጎጂችም እንዲደረግላቸው ከጠየቁ ይደረግላቸዋል)፡፡

**ፍርድ** ፡- ለተጎጂዎች ( ወይንም ተጎጂዋ ፍርድ ቤት ቆማ ቃሏን ለመስጠት እድሜዋ የማይፈቅድ ከሆነ ለጠባቂዋ/ለሞግዚቷ) ስለ ፍርድ ሂደቱና ውጤቱም ምን እንደሚመስል ሊነገራቸው፤ በየጊዜውም ስለተደረሰበት ሁኔታ እንዲያውቁ በማድረግ በህግ ስርአቱ ላይ እምነት እንዲኖራቸውና ጉዳያቸውን እስከመጨረሻው እንዲከታተሉት ማስቻል፡፡

### የሕጻናትን ጉዳይ ለመከታተል መከተል የሚገቡ ደንቦች

ከአጠቃላይ መርሆው በተጨማሪ የሕጻን ተጎጂዎችን ጉዳይ ለመከታተል የሚከተሉትን ደንቦች መከተል ያስፈልጋል፡-

- ✓ የሕጻን ተጎጂዎች በሚረዱት ቋንቋ ግንኙነት ማድረግ ይኖርባቸዋል
- ✓ ማንኛውም ህፃን የሷ ብስለት አስከፈቀደላት ድረስ የሚታወቅና ተቀባይነት ያለው የምስክርነት ቃል መስጠት ትችላለች ተብሎ መታሰብ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ለተጎጂዋ ህፃን የሚደረግ ምርመራ በተለየ ገለልተኛ ክፍል ውስጥ በተወካይዋ እየተረዳች ጥቃቱን ፈጽሟል የተባለው ሰው ማየት በማይችልበት ሁኔታ መከናወን አለበት፡፡ ለተከሳሹ መብት መከበር ትኩረት ስላለመደረጉ ክትትል በሚደረግበት ወቅት በህፃኗ የግል ሕይወት ላይ ጣልቃ የመግባት ሁኔታ እንዳይፈጠር በሚቻለው ደረጃ የተገደበ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ✓ የሕጻኗ የምስክርነት ቃል በሚሰማበት ወቅት በማህል የእፎይታ ጊዜ ሊሰጣት ይገባል፡፡
- ✓ የፍርድ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በፍርድ ሂደቱ ወቅት በተጎጂዋና በተከሳሹ መካከል ምንም አይነት ንክኪ መፈጠር አይኖርበትም፡፡

## ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የሚሰጥ የምክክር አገልግሎት

ሁሉም ባለድርሻዎች ከተበዳዮች ጋር የመገናኘት አጋጣሚ በተፈጠረበት ወቅት ሁሉ የምክክር አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ የምክክር አገልግሎቱ ፡-

- *አንድ ለአንድ/በግል ፡-* አማካሪውና ተገልጋዩ ብቻ ፊት ለፊት በመቀመጥ
- *በቡድን ፡-* በምክክሩ ወቅት በርከት ያሉ ሰዎች ፊት ለፊት በመቀመጥ በተሳተፉበት ሁኔታ
- *በስልክ ፡-* ተገልጋዩ ከምክክር ባለሙያው ጋር ሳይተያይ በስልክ
- *በቀጥታ መስመር/* በኢ-ሜል አማካይነት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡

### ሁሉም የዚህን ሰነድ ባለድርሻ የሆኑ አካላትን ወክለው የሚሰሩ የምክክር ባለሙያዎች የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች መከተል ይኖርባቸዋል፡-

- የምክክር አገልግሎቱን ከመስጠታቸው በፊት ጥቃቱ የሚያስከትለውን ተፅእኖ በቅድሚያ መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡
- ከተገልጋዮች ጋር ትውውቅ ማድረግና በማንኛውም ጊዜ ተበዳዮችን በስም መጥራት
- ተገልጋዮች የሚናገሩትን በጥሞና ማዳመጥና መከታተል
- ተገልጋዮች በተዝናና ሁኔታ ውስጥ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- ተገልጋዮች ሊወያዩባቸው በሚፈልጉት ጉዳይ ላይ ሀሳብን ማካፈል
- ለተገልጋዮችን ማክበር፣ የፍቅርና የአክብሮት ስሜት መስጠት
- ለተገልጋዮች እውነተኛና ታማኝ በመሆን የደንበኞችን ሚስጥር መጠበቅ
- ተገልጋዮች በግልጽ ሊረዱትና ሊገባቸው የሚችሉትን ቋንቋ መጠቀም
- ለተገልጋዮች አነጋገርና ስሜት ትኩረት በመስጠት ሀሳብን ማካፈል
- ተገልጋዮች የተሳሳተ አመለካከትን፣ እምነትንና አስተሳሰብን አስወግደው በራሳቸው በመተማመን መንፈስ ጠንካራነትን እንዲያጎለብቱ ድጋፍ ማድረግ
- ለተገልጋዩዋ ፈታኝ ለሆኑ ችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ያሉትን አማራጮች በማመላከት የአማራጮቹን ጠንካራና ደካማ ጎን ማስረዳት፡፡
- ተገልጋዮች ለችግሩ ማቃለያ በቀረቡ አማራጮች ላይ የራሳቸውን ውሳኔ መወሰን እንዲችሉ መርዳት

- ተገልጋዮች ውሳኔያቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ ማድረግ
- ለተገልጋዮች ከወሲባዊ ጥቃት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች መስጠት
- ለተገልጋዮች ተከታታይነት ያለው የምክክር አገልግሎት መስጠት
- ጉዳቱ የከፋና ከአማካሪው ችሎታ በላይ ሆኖ ሲገኝ ወደ ሚመለከተው ባለሙያ ማስተላለፍ
- ተገልጋዮች ውሳኔ ከወሰኑ በኋላ ተግባራዊ ማድረጋቸውን እና ከችግራቸው ማገገማቸውን (መፈወሳቸውን) መከታተል፡፡

## የስነልቦናዊና የማህበራዊ አገልግሎት አይነቶችና ደረጃዎቻቸው

ከሚከተሉት የስነልቦና አገልግሎት አይነቶች መካከል አንደኛው የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች እንዲያገግሙ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል

1. የቤተሰብ ምክክር አገልግሎት ፡-አማካሪው (ካውንስለሩ) ከተበዳዩዋ ቤተሰብ አባላት ጋር በመሆን የቤተሰቡን ሥርአት፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችን፣ እንዲሁም የአካባቢውን ሁኔታ ተሳቢ በማድረግ ለተበዳዩዋ ጥቅም ሲባል የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡

2. ድጋፍ ሰጪ ቡድን ፡- ተመሳሳይ ችግር ባጋጠማቸውና በጎ ፍቃደኛ በሆኑ ተሳታፊዎች አማካኝነት የሚመሰረትና ለአዲስ ተሳታፊዎች ክፍት ወይም ዝግ በማድረግ አገልግሎት የሚያገኙበት ነው፡፡

3. የቡድን ምክክር አገልግሎት፡- በአማካሪውና ተመሳሳይ ችግር ባለባቸው ተገልጋዮች መካከል የሚከናወን የምክክር አገልግሎት ሲሆን የቡድኑ አባላት ልምድን በመለዋወጥ፣ ከሌሎች ተሞክሮ በመማር፣ የባለሙያውን ሙያዊ ድጋፍ በማግኘት የእርስ በእርስ መስተጋብር የሚተገበሩበት ሂደት ነው፡፡

4. የጨዋታ ህክምና፡- አሻንጉሊቶችን፣ሌሎች ቁሳቁሶችን ወይንም ተገቢ የሆኑ የመግባቢያ ዘዴዎችን ፣ ሕግና ስርአት ያላቸው ጨዋታዎችን በመጠቀም የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት ነው፡፡ የስእልና የቀለም ቅብን በመጠቀም ስነ ጥበባዊ ህክምናም ይሰጣል፡፡ በዚህ አገልግሎት ውስጥ ዋናው መርህ

"ህፃኑ ይመራል፤ አማካሪው ይከተላል"» የሚለው ነው፡፡ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፡-

- በአሸዋ የተሞላ ሳጥን/ገበታ(ትሪ)
- ትክክለኛውን የሰውነት ቅርፅ የሚያሳዩ አሻንጉሊቶች
- የተለያዩ ቀለም ያላቸው ስዕሎችና ወረቀቶች
- የተለያዩ መጫዋቻዎችና (ጌሞች)
- የተለያዩ የእንስሳት ምስሎች (ፐፔት) ናቸው፡፡

ችግሩን ለመቋቋም የሚያስችላቸውን ስሜት፣ አስተሳሰብና ባህሪ እንዲያውቁ፣ እንዲረዱና እንዲያስተካክሉ ድጋፍ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡

5. የስነአዕምሮ ምክር አገልግሎት፡-በአማካሪው (በካዉንስለሩ) እና በተገልጋዩዋ መካከል የሚመሰረት ግንኙነት ሲሆን ተገልጋዩዋና ቤተሰቦቿ ችግሩን ለመቋቋም የሚያስችላቸውን ስሜት፣ አስተሳሰብና ባህሪ እንዲያውቁ፣ እንዲረዱና እንዲያስተካክሉ ድጋፍ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡

ወሲባዊ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሰዎችን ስነ-ልቦናዊ ጥንካሬ የማዳበር ስራ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የመልሶ ማቋቋምና/ማህበራዊ ተሀድሶ ስራ ባልሰለጠኑ ሰዎች በአብዛኛው ይሰራል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች የባለሙያ እገዛ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ የነኝህ አሰራሮች ዋና ዋና አላማዎች፡-

- በሕጻናቱ፣ በጓደኞቻቸውና በሰራተኞች መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲፈጠር ማስቻል ሲሆን ይህም ተገቢውን ክትትል፣ ቁጥጥር፣ እንክብካቤና ጥበቃ በማከናወን እንዲሁም ከሌሎች ሕጻናት ጋር በስፖርታዊ ክንዋኔዎች፣ በሚያዝናኑ ጨዋታዎች፣ ተረቶችና በሌሎች የመዝናኛ ዘርፎች የመሳተፍ እድል እንዲያገኙ በማድረግ የሚከናወን ይሆናል፡፡
- ሕጻናቱ በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች ላይ እምነትና ደህንነት/ምቾት እንዲሰማቸው በማድረግ በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ማዳበር፡፡ በምክክር አገልግሎቱ ሂደት ከቤተሰብ ጋር ወይንም በጊዜያዊ ማረፊያ ጣቢያ ውስጥ የሚገኙ ቡድኖች ለራስ ክብር የመስጠትና በራስ የመተማመን ክህሎታቸውን መልሰው እንዲያጎለብቱ ይደረጋል
- ራስን በራስ በማስተማር፡- ተጎጂዎች ራሳቸውን ብሎም እንደቤተሰብና ጓደኛ የመሳሰሉና ለነሱ አስፈላጊና ቅርብ የሆኑ ግለሰቦችን ሚና እንዲገነዘቡና ራሳቸውን ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር እንዴት በተሻለ ሁኔታ አስማምተው መኖር እንዳለባቸው ሊማሩ የሚችሉበትን እድል የሚፈጥርላቸው ነው፡፡
- የባህሪ ለውጥ ማምጣትና ራስን ከሁኔታዎች ጋር የማስማማት ብቃት ለማዳበር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠር ፡- የዚህ ፕሮግራም ዓላማ ጠቃሚ መርሆዎችንና መልካም ተምሳሌቶችን/ሞዴሎችን በማሳየት እንዲሁም በምን መልኩ የግል ባህሪያቸውን ማነጽና ለራሳቸው ያላቸውን አተያይ በአዎንታዊ መልኩ መገንባት እንዳለባቸው ምክር በመለገስ የሕጻናቱ ቀጣይ ሕይወት ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ማሳረፍ ነው፡፡በተጨማሪም ተጎጂዋ ስለ መልካም ባህሪና ስለሚያስገኘው የሕይወት ለውጥ በተማረችና በተረዳች ቁጥር አፍራሽ ወይም ተፃራሪ የሆኑ ዝንባሌዎችን እያስወገደች መምጣት ያስችላታል፡፡
- በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ የቆዩ ሕጻናትን ወደ ቤተሰብ የማቀላቀልም ሆነ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መስተጋብር እንዲፈጥሩ የማድረግ ሂደት ራሱን የቻለ መርህና ተግባራት አሉት፡፡ ተግባራቱም ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሲኖሩት እነርሱም
    - ቅድመ መልሶ ማቋቋምና
    - ድህረ ማቋቋም ናቸው

1. የቅድመ ማቀላቀልና ማቋቋም ተግባራት
    - የወላጆችን (የአሳዳጊዎችን) አድራሻ ማፈላለግና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ማጥናት
    - የማቀላቀል ተግባራዊ ዕቅድ ማዘጋጀት
    - ሕጻኗን ማዘጋጀት
    - ቤተሰብን ወይንም ዘመድን ዝግጁ ማድረግ
    - ሕጻኗ ወደ አዲስ መኖሪያ ቤት ለመግባት ዝግጁ እንድትሆን ማድረግ

- ሕጻኑ/ኗ ከቤተሰብ ፣ ከአሳዳጊ ወይም በጊዜያዊ መጠለያ ከተቀላቀለች በኋላ በምልልስ-ክትትል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ማየትና መከታተል
- ለተቀላቀለችው ሕጻን ቀጣይነት ያለው ድጋፍ መስጠት
- ጉዳቱ ለደረሰባቸው ሕጻናት የተለያዩ የአቅም ግንባታ/የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠናዎችን መስጠት
- ወደ ቤተሰብ የተመለሱ ሕጻናትን ሁለንተናዊ አቅም መገንባት
- ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸው ወደ ቤተሰብ የተመለሱ ሕጻናት የሚከተሉት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ማግኘት ይኖርባቸዋል፡-
    - ✓ የሕይወት ክህሎት ስልጠና
    - ✓ መሰረታዊ የንግድ ክህሎት ስልጠና
    - ✓ በራስ የመተማመን ብቃት ስልጠናዎች ናቸው፡፡

## 4.3. ተጎጂዎች የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ (የአንድ መስኮት አገልግሎት) የሚያገኙበት አካሄድ

ተጎጂዋ ስለገጠማት አጋጣሚ ለአንደኛው ተዋናይ ሪፖርት ካደረገች (የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ ውስጥ በሚሰጥበት መዐከል ባለሙያ/ሰራተኛ ካልሆነ) ተጎጂዋ አጀብ ተደርጎላት የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ ወደሚሰጥበት (በአቅራቢያው የሚገኝ ከሆነ) መላክ ይኖርባታል፡፡

### የሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም

ሀ) ተጎጂዋ የተሟላ አገልግሎት በአንድ ማዕከል ከሚሰጥበት ቦታ እንደደረሰች በጣቢያው አስተባባሪ ታጅባ ወደ ማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው ተወስዳ ተገቢውን የምክክር አገልግሎት እንድታገኝ ድጋፍ ይደረግላታል፡፡ በማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛው ተጎጂዋ እንድትረጋጋ የምክክር አገልግሎት እንድታገኝ ከተደረገ በኋላ በቀጣይ በማዕከሉ ውስጥ ስለምታገኛቸው አገልግሎቶች ገለጣ ይደረግላታል፡፡ ለ) የምክክር አገልግሎቱን ካገኘች በኋላ በማዕከሉ ሐኪም ምርመራ እንዲደርግላትና ሕክምና እንድታገኝ ይደረጋል፡፡

ሐ) ተጎጂዋ ሕጻን ከሆነች በሐኪሙ/ሟ ስለሚደረግላት ምርመራ ተጎጂዋ ባለችበት ቤተሰቦቿ ማብራሪያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በማስከተልም ህክምናው ከመካሄዱ በፊት የስምምነት ቅፅ ተፈርሞ ለሀኪሙ/ሟ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

መ) ተጎጂዋ በህክምናው ምርመራ ወቅት በቤተሰቦቿ አባል ወይንም በመረጠችው ሌላ ሰው መታጀብ እንደምትፈልግ በሀኪሟ ትጠየቃለች፡፡ ሠ) ሀኪሙ/ሟ የህክምና ምርመራውን በመቀጠል ለህግ ማስረጃ የሚሆኑትን የምርመራውን ውጤቶች ሪፖርት በማዕከሉ ውስጥ ለሚገኝ የፖሊስ መኮንን ያስተላልፋል፡፡ ረ) ተጨማሪ የምክክር አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው ከኬዝ ማኔጀሩ ጋር በመሆን ከሌላ የምክክር አገልግሎት ሰጪ ተቋም አገልግሎቱን የምታገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፡፡

ሀ) ከሕክምና ምርመራው በኋላ በፖሊስ መኮንኑ ስለ አጠቃላይ ሂደቱ ለተጎጂዋ ወይም ለቤተሰቧ ገለፃ ይደረጋል፡፡ ለ) ተጎጂዋ ቃሏን በምትሰጥበት ክፍል ውስጥ የቤተሰቧ አባል ወይንም ጓደኛዋ ከአጠገቧ እንዲገኙላት ከጠየቀች የፖሊስ መኮንኑ ምርመራውን የማያጨናግፍ ወይንም አደጋ ላይ የማይጥል ሆኖ ካገኘው እንዲገኙላት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

ሐ) ተጎጂዋ ቃሏን ለመስጠት ፍቃደኛ ከሆነችና ከቻለች የፖሊስ መኮንኑ ከአቃቢ ሕግ ጋር በመሆን ቃሏን ይቀበላል፡፡ የማትችል ከሆነ ግን ወደ ማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው/ዋ ተልካ እንድትረጋጋ ድጋፍ ተደርጎላት ቃሏን ተረጋግታ እንድትሰጥ ይደረጋል፡፡ መ) ተጎጂዋ የምትሰጠው ቃል ስለ አጋጣሚው ሁኔታ መረጃዎችን ያካተተ ቦታውን፣ ሰአቱን፣ ጥቃቱን ያደረሰውን ሰው ማንነት(ከታወቀ)፣ ማንኛውንም አይነት የመለያ ምልክት፣ ጥቃት ፈጻሚው የተጠቀመበት ማንኛውም አይነት መሳሪያ፣ ወዘተ. ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሠ) ተጎጂዋ ቃሏን ከሰጠች በኋላ ወደ ቤቷ እንድትመለስ ይደረጋል፡፡ ወደ ቤቷ መመለሷ ተጠቂዋን አደጋ ላይ የሚጥላት ከሆነ ጉዳይ አስፈጻሚው ከፖሊስ መኮንኑ ጋር በመተባበር መጠለያ የምታገኝበትንና ማህበረሰባዊና የስነልቦና አገልግሎት እንድታገኝ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ ረ) ከቃል መቀበል በኋላ ፖሊሱ ሁሉንም ጠቃሚ ግኝቶች፣ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ የህክምና ማስረጃዎችን፣ በሷ/ሱ ምርመራ የተገኙትን ሁሉ በፋይሏ ውስጥ በማሰባሰብ ለአቃቤ ሕጉ ያስተላልፋል፡፡

### 1. የተሟላ አገልግሎት በአንድ ማዕከል በሚሰጥበት ውስጥ የሚያስፈልግ የሰው ሐይል

1. የጣቢያው አስተባባሪ
2. ኬዝ ማኔጀር
3. የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ
4. የሕክምና ባለሙያ (ሀኪም/ነርስ)
5. ፖሊስ
6. አቃቤ ሕግ
7. አስተርጓሚ (የምልክት ቋንቋን ጨምሮ)

### 2. የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ በሚሰጥበት ውስጥ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

1. የሕክምና መሳሪያዎች
2. ወንበርና ጠረጴዛ
3. ሌሎች መሳሪያዎች የፅሁፍና የመገናኛ መሣሪያዎችን የመሳሰሉት

### 3. የተሟላ አገልግሎት በአንድ ጣቢያ በሚሰጥበት ውስጥ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

1. የመቆያ ክፍል/ክፍሎች፡- ተጎጂዎች የፖሊስ መኮንን ወይንም የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ እስኪመደብላቸው ድረስ የሚቆዩበት፡፡
2. የምርመራ ክፍል/ክፍሎች፡- ሀኪሞች ምርመራ የሚያካሂዱበትና ህክምና የሚሰጡበት ክፍል

3. የቃል መቀበያ ክፍል/ክፍሎች፡- ፖሊስና አቃቤ ሕግ ምርመራ የሚያካሂዱበትና የተጎጂዋን ቃል የሚቀበሉበት፡፡
4. ለማህበራዊ አገልግሎት ሠራተኞች የተለየ ክፍል፡- የማህበራዊ አገልግሎት ሠራተኛው ተጎጂዋ ቃሏን ከመስጠቷ በፊትና በኋላ የስነልቦና ድጋፍ የሚሰጡበት
5. ለአስተባባሪዎችና ጉዳይ አስፈጻሚዎች ክፍል/ክፍሎች
6. መፀዳጃ ቤት/መታጠቢያ ክፍሎች

## የአቃቤ ህግ አፈጻጸም

አቃቤ ሕጉ ለጉዳዩ አስፈላጊ የሆኑ የህክምና መረጃዎችና የሕግ ማስረጃዎችን ከፖሊስ መኮንኑ ካሰባሰበ በኋላ በ 4.2.3 ላይ በሰፈረው የአቃቤ ህጉ አሰራር መሰረት ይተገበራል፡፡

# ክፍል-5
# ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል

## 5.1 መከላከል

በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት ከማህበረሰቡ ዕሴቶች፣ እምነት፣ ወግና ስርአት ጋር በከፍተኛ ደረጃ ስር የሰደደና የተቆራኘ በመሆኑ የመከላከል እስትራቴጂውም በዋናነት ከማህበረሰብ ንቅናቄና ከአቅም ግንባታ ጋር በማስተሳሰር የባህሪ ለውጥ በግለሰብ፣ በቤተሰብና ብሎም በሰፊው ህዝብ ደረጃ እንዲመጣ መስራት አሰፈላጊ ይሆናል፡፡ እስካሁን በተለያዩ አጋር ድርጅቶች የተከናወኑ መልካም ተሞክሮዎችን በማጎልበት ማህበረሰቡን የማንቀሳቀስ ጥረት ስልታዊ በሆነ አሰራር በበለጠ ተጠናክሮ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ በአብዛኛው የተመቻቹ የውይይት መድረኮች ጠቀሜታ በተወሰኑ አካባቢዎች የተወሰኑ ሰዎችን እና አካላትን ብቻ መድርስ የሚችሉ በመሆናቸው በሀይማኖት ተቋማት የትምህርት መድረኮች፣ በእድሮች፣ ባህላዊና ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና በሴቶች የልማት ሰራዊት አማካኝነት የስርዓተ ፆታ እንቅስቃሴዎችን፣ ሌሎች ሕዝባዊ መሰረት ያላቸውን አካላት በማስተባበር መልዕክቶች በስፋት የሚሰራጩበትን አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ዋናው ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከል አላማ የተጠናከረና ቀጣይነት ያለው የማህበረሰብ ንቅናቄ በመፍጠር በወሲባዊ ጥቃት ላይ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል ደረጃ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡

### የህዝብ ግንዛቤ መፍጠርና የማሕበረሰብ ንቅናቄ

- በወሲባዊ ጥቃት ላይ ያልተቋረጠ የማነቃቃትና የህዝብ ግንዛቤን የማጎልበት ስራ መስራት
- በመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የተቀናጀ የማነቃቃትና ግንዛቤን የማበልፀግ እንቅስቃሴን ማስተባበር
- በሴቶች የልማት ሰራዊት፣ የሴቶች ማህበራትንና በሥርዓተ ፆታ እንቅስቃሴዎች አማካኝነት በወሲባዊ ጥቃት ዙሪያ ሕብረተሰቡን ማስተማር
- በሁሉም ደረጃ በሚደረጉ የፀረ-ወሲባዊ ጥቃት እንቅስቃሴ የወጣት ወንዶችንና የጎልማሳ ወንዶችን ተሳትፎ/አስተዋጽኦ ማጠናከር
- በማንኛውም አይነት በሴቶች ላይና በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመከላከል የጋራ የሆነ ስምምነት እንደፈጠር የማህበረሰብ ውይይት መድረኮችን ማመቻቸት
- ሕግን በጎልማሶች የትምህርት ፕሮግራሞችና በመደበኛ ትምህርት በማካተት ለህዝቡ፣ ለህዝባዊ ማህበራት፣ ለማህበራት፣ ለማህበረሰቡና ለሴቶች ቡድኖች፣ ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ኮሚቴዎችና በወሲባዊ ጥቃት ላይ ለሚሰሩ የትምህርት ቤቶች ክበባት እንዲዳረስ ድጋፍ ማድረግ፡፡
- ለወጣቶች ምቹና ተስማሚ የሆነ የሥነ-ተዋልዶ ትምህርትና የመረጃ አቅርቦት አጠቃቀምና ተደራሽነትን ማስፋፋት
- በተወሰነ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ የባህሪ የግብብነት ስትራቴጂዎችን ቀምሮ ማዘጋጀትና
- ለመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ የማሳደግ ስልጠና በማዘጋጀት በወሲባዊ ጥቃት ላይ መረጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ስርጭቱ እንዲጨምር በማድረግ የህብረተሰቡን ሚና በመከላከልና ብሎም ለማስወገድ ለማስተባበር መገናኛ ብዙሀንን ለማህበረሰብ ንቅናቄ መጠቀም፡፡

### ተቋማዊና ማሕበረሰባዊ አቅም ማጎልበት

- የፖሊስና የሕግ አስፈጻሚ አካላትን፣ የህዝባዊ ማህበራትን ፣የሀይማኖት ተቋማትን፣ የሴቶችና ወጣቶች ማህበራትን፣ የጎጂ ልማድ አስወጋጅ ኮሚቴዎችን፣ የሴቶች ልማት ሰራዊትን፣ የስርአተ ጾታ እንቅስቀሴዎችን፣ የማህበረሰብ የለውጥ አካላትንና ጤና ተቋማትን ወዘተ. አቅም በማጎልበትና በማስፋፋት በፀረ-ወሲባዊ ጥቃት እንቅስቃሴ የበለጠ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማጠናከር፡፡
- ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ብሎም ለማስወገድ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በመለዋወጥ እርስ በእርስ መማማርን እንዲያዳብሩ የስብሰባ መድረኮችን ማመቻቸት፡፡
- ጠቀሜታቸው የተረጋገጡ ግኝቶችን ላስመዘገቡ አሸናፊዎች፣ ተምሳሌታዊ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ሞዴሎች፣ አስተማሪዎች፣ ትርጉም ያለው አዎንታዊ የለውጥ ሀዋሪያዎችን (ኤጀንቶች ) የማነቃቂያ ሽልማቶችን በማቅረብ ማበረታታት፡፡

## 5.2 በጤናው ዘርፍ ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች 75 % የሚሆነውን የስራ ጊዚያቸውን ከቢሮ ውጭ በቤት ለቤት በመዟዟር እንዲሰሩ ይጠበቃል፡፡ በሌሎች የልማት ስራዎች በመሳተፍ መልካም ተሞክሮ ያስመዘገቡ ግለሰቦችን፣ በህብረተሰቡ ተቃባይነትንና ከበሬታ ያላቸውን ሞዴል ቤተሰቦችን በመለየትና ስልጠና በመስጠት ያደራጃሉ፡፡ ሞዴል ቤተሰቦች የጤና መረጃዎችን በማሰራጨት የሚፈለገው የባህሪ ለውጥ እንዲስፋፋ ለማድረግ አይነተኛ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በማህበረሰብ ደረጃ ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በተጨማሪ ከህብረተሰቡ ጋር ትስስር ያላቸው ቡድኖችን የጤና ልማት ሰራዊቶች ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን እንደ ድልድይ በመሆን ከህብረተሰቡ ጋር ያገናኛሉ፡፡ የጤና ትምህርትና የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጠት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ቀዳሚ ተግባሮች ሲሆኑ በጤና ልማት

ሰራዊቱ እየታገዙ ተቀዳሚ የወሲባዊ ጥቃት መከላከል አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለመስጠት ምቹ ኢጋጣሚን ይፈጥርላቸዋል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የጤና ልማት ሰራዊቶች ህብረተሰቡ ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከል ተሳታፊ እንዲሆን በማስተባበር ደረጃ አይነተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ በተለይ በሚከተሉት ላይ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡-

- ከሥርዓተ ፆታ ጋር ለተያያዙ ጉዳዮችና ለወሲባዊ ጥቃት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን አስተሳሰቦች፣ ባህል፣ ወግና ስርአት ለመቀየር የተጠናከረ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን መፍጠር፡፡
- በወሲባዊ ጥቃት ላይ የህብረተሰቡን ምላሽ ማሻሻል
- ግጭት *“ የቤተሰብ ጉዳይ ነው ”* የሚልን የተዛባ አስተሳሰብ ማስወገድ
- ተጎጂዎች ድጋፍ የመጠየቅን ልምድ እንዲያዳብሩ ማበረታታት
- አገልግሎት ሰጪዎች ድጋፍ እንዲያደርጉ ማበረታታት
- በአገልግሎት አቅራቢዎችና በማህበረሰቡ መካከል ህብረት እንዲፈጠር ማበረታታት
- ሴቶች ለተለያዩ አገልግሎቶች ያላቸውን ተደራሽነት ማሻሻል
- በሂደት ላይ ባሉ ፕሪጀክቶች በወሲባዊ ጥቃት ላይ ህብረተሰቡን የማስተባበር ስራን ለመስራት ቅድሚያ የሚሰጡ አካላትን ማበረታታት

- ወሲባዊ ጥቃትን የመሸከም(በትዕግስት የማለፍን) ሁኔታ ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶችን በወጣት ወንዶችና በጎልማሳ ወንዶች ላይ በመስራት ማገዝ
- ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በማስተባበር ለሚሰሩ ፕሮግራሞች የመዋዕለ ንዋይ ድጋፍ ማድረግ
- በሁሉም የህብረተሰብ ደረጃዎች ላይ አጋርነትን ለመመስረት ማስተባበር
- ተጎጂዎች ለአገልግሎቶች ያላቸውን ተደራሽነት ለማሻሻል የሚደረግን ጥረት መደገፍ

በተጓዳኝ የጤና እክስቴንሽን ሰራተኞችና የጤና ልማት ሰራዊቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ቦታና ከበሬታ በተመረጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትምህርት በመስጠት ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በማህበረሰቡ ውስጥ የተወሰኑ የወንዶችን ቡድን በማነሳሳት ስለ ወንዶች ህብረት መፍጠርና በስርአተ ጾታ ሚናቸው ላይ በመነጋገር ከሴቶች ጋር ባላቸው ግንኙነት ጠቀሜታ ያለው ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ ማስተማር ይችላሉ፡፡ እነኝህ አካላቶች በተጨማሪ ወንዶች እሴቶቻቸውን እና ባህሪያቸውን በማጤን አፍራሽ በሆኑት ላይ ለውጥ ለማምጣት እንዲሰሩ ማድረግም ይችላሉ፡፡

## 5.3. ይሄንን ደረጃውን የጠበቀ የአተገባበር ስርአት ሰነድ ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ

በአጠቃላይ ይሄ ሰነድ ውጤታማና ጠቀሜታ ሊኖረው የሚችለው ህብረተሰቡ ለአገልግሎቶች ተደራሽነት ኖሮት ስምምነት በተደረገባቸው አሰራሮች ተጠቃሚ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ የሰነዱ ቅጂ ለዋና ዋና አጋር ድርጅቶችና አካላት የሚከፋፈል ሲሆን በተጨማሪ ለበርካታ አካላት ለማዳረስ አውደ ጥናቶች ይካሄዳሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ሰነዱን ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ለማድረግ የሚከተሉት መረጃዎች እንዲተላለፉ ይደረጋል፡-

- ድጋፍ ለማግኘት የት መሄድ እንዳለባት
- ምን አይነት አገልግሎቶች እንዳሉና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል
- ከባለድርሻዎቹ ምን እንደሚጠበቅ፣ የሀላፊነት ግዴታቸውና ወሰን እምን ድረስ እንደሆነ፣ በቅብብሎሽ አሰራሩና ጠቀሜታ ላይ ስለሚኖራቸው ሚና
- የግል ሚስጥር በአስተማማኝ ሁኔታ እንዴት እንደሚጠበቅ ከተለያዩ የህብረተሰብ ቡድኖች ከሴቶች፣ ከወንዶች፣ ከልጃገረዶች፣ ከወጣት ወንዶች ጋር በመገናኘት መረጃዎችን ያስተላልፋሉ፤

ለጥያቄዎቻቸው መልስ ይሰጣሉ፡፡ ለአገልግሎት ጣቢያዎች የመግቢያ ምልክት መስጠት፤ ሪፖርቶችንና የቅብብሎሽ ቅጾችን በአካባቢው ቋንቋ ወይንም በስእላዊ መግለጫ ማዘጋጀት፡፡ ይሄ የአንድ ጊዜ የማሳወቅ ወይንም መረጃ የመስጠት ዘመቻ አይደለም፡ ፡ በዚህ ከፍተኛ ጠቀሜታ ባለው ጉዳይ መረጃዎችንና የድጋፍ አገልግሎት ፍላጎትን ለማሟላት ሳይቆራረጥ በቀጣይነት መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የጤና ልማት ሰራዊቶች ከሌሎች የህብረተሰብ ተወካዮች ጋር በመሆን ተጠቂዎችን ለመድረስ ምቹ በሆነ ሁኔታ ላይ ስለሚገኙ መረጃዎችን በቀጣይነትና በውጤታማነት ለማሰራጨት ያስችላል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች በሙሉ ለተጎጂዋ ወይንም ለእርሷ ቤተሰቦች/ጠባቂዎች በቀላሉ መረዳት በሚያስችል የአከባቢው መግባቢያ ቋንቋ ተዘጋጅተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

# አዝል- 1

## ለህክምና የምክክር አገልግሎት የስምምነት ቅጽ

------------------------------------------------ (የጤና ባለሙያው/ዋ ስም ይስፈር) የምርመራው አሰጣጥ ስርአት፣ የመረጃው አሰባሰብና ውጤቶቹ ለፖሊስ እና/ወይንም ለፍርድ ቤት እንደሚላክ ማብራሪያ ተሰጥቶኛል፡፡

እኔ ------------------------------------------------ (የህመምተኛው/ዋ ስም ይስፈር) በሚከተሉት ዝርዝሮች ላይ ተስማምቻለሁ፡፡

*(በተመረጠው ላይ ምልክት ያድርጉ)*

- ምርመራ ፤ በመራቢያ አካልና በፊንጢጣ ላይ የሚደረግን ምርመራ ጨምሮ ይደረጋል፡፡
- ማንኛውም አይነት የጤና ችግር መፈጠሩን ለማወቅና ለመመርመር ናሙና ይሰበሰባል፡፡
- ለወንጀል ምርመራ ናሙናዎች ይሰበሰባሉ፡፡
- ፎቶ ግራፍ ይወሰዳል፡፡
- የቃልና የፅሁፍ ሪፖርቶች ለፖሊስና ለሌሎች ምርመራ አካላት ይቀርባል፡፡
- ለማንኛውም ለተገኙ የጤና ችግሮች ሕክምና ይሰጣል፡፡

የታካሚው (የወላጆች/የጠባቂዎች) ፊርማ ወይንም ምልክት---------------------------------

የምስክር ፊርማ ------------------------------------------------

ቀን ------------------------------------------------

*ምንጭ ፡- ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የህክምና ክትትል መመሪያ ©የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት (2003)*

# እዝል-2

## የቅብብሎሽ አገልግሎት ቅፅ

ያስተላለፈው አካልና ክፍል ---------------------------------------------

ለ (የተላለፈለት አካል/ክፍል) -------------------------------------------

የተጎጂዋ ስም ወይንም የግለሰቧ መለያ ቁጥር ---------------------------------- እድሜ------------- ጾታ----

አድራሻ ፡- ክልል-------------------- ክፍለ ከተማ/ዞን --------------- ወረዳ/ቀበሌ------------

የቤት ቁጥር----------ስልክ ቀጥር-------------የተላለፈበት ቀንንና ሰአት------------

ተጎጂዋ ህፃን ከሆነች የድጋፍ ሰጪው/ዋ ስም-------------------------------

ግንኙነታቸው/ዝምድናቸው---------------------------

<u>የአደጋው አጋጣሚ</u>

ግልፅ በሆነና በተብራራ ሁኔታ ተለይተው የታወቁ ችግሮችን ( የአካባቢውን ሁኔታ መከለስ፣ በትክክል የተፈጠረው ሁኔታ ፣ በቀጣይ ምን እንደተፈጠረ)

---

---

---

ምን ተደረገ፡-

---

---

---

ተጎጂዋ የተላለፈችበት ምክንያት ፡-

---

---

---

በተጨማሪ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎችና የታቀዱ እርምጃዎች ፡-

---

---

---

---

ያስተላለፈው ክፍል ፡- -------------------------------------------------------------------------------------------------

ያስተላለፈው ግለሰብ ፡- -------------------------------------------------------------------------------------------

ፊርማ ፡- ----------------------------------------------------------------------------

# አባሪ- 3

## የወሲባዊ ጥቃት የሕክምና ምስክር ወረቀት

የጤና ተቋሙ ስም --------------------------------------------------- የታካሚው ስም ------------------------------ፆታ----------

ዕድሜ --------- ካርድ ቁጥር --------------- ስራ -------------------------------የጋብቻ ሁኔታ--------------------ቀን -----------

የጠባቂ/የሞግዚት ስም (ተጎጂዋ/ው ቃል ለመስጠት የማትችል ወይም የአካል ጉዳተኛ ከሆነ/ች)----------------------------------

የጥቃቱ አፈጻጸም (በተቻለ አቅም በተጎጂው/ዋ ቃላትና አገላለፅ)__________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

የጤና ተቋም ምርመራ ውጤት (በተጎጂዋ የህክምና ካርድ ላይ በሰፈረው መሰረት በአካል፣ በሀፍረተ ስጋ ወይም በፊንጢጣ ላይ የደረሰ ጉዳት)____________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት __________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ማጠቃለያ ____________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ሕክምናውን የሰጠው ባለሙያ ስም __________________________________

ፊርማ ______________________

*ይህ የምስክር ወረቀት በሶስት ቅጂ (ኮፒ) ይዘጋጃል፡፡ ዋናው ቅጂ ለፍርድ ቤት እንዲቀርብ ለፖሊስ ይላካል፡፡ ሁለተኛው ቅጂ ለተጎጂዋ ይሰጣል፡፡ ሶስተኛው ቅጂ ከተጎጂዋ የህክምና ካርድ ጋር ተያይዞ ይቀመጣል፡፡ የምስክር ወረቀቱ ሚስጥራዊነቱ በአስተማማኝ ሁኔታ ተጠብቆ መሀተም ተደርጎበትና ተፈርሞበት ለፖሊስ መላክ ይኖርበታል፡፡*